https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፸፫
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፱ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No.73
ADDIS ABABA, 26th July, 2017.

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፷/፪ሺ፱ ዓ.ም
የባቡር ትራንስፖርት አስተዳደር አዋጅ
ገፅ..... ፱ሺ፯፻፫፫

CONTENT

Proclamation NO.1048/2017
Railway Transport Administration Proclamation
Page..... 9773

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፷/፪ሺ፱

የባቡር ትራንስፖርት አስተዳደር አዋጅ

የባቡር ትራንስፖርት ተስፋፍቶ የሀገሪቱን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚደግፍ አማራጭ የትራንስፖርት ንዑስ ዘርፍ ለማድረግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር የሚገባ በመሆኑ፤

የባቡር መሰረተ-ልማቶች የሚገነቡበትና አገልግሎት ላይ የሚውሉበት ሀገር አቀፍ ደረጃ የሚወሰንበት ሥርዓት መዘርጋት የሚያስፈልግ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፪) (ሐ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡-

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የባቡር ትራንስፖርት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፷/፪ሺ፱ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

PROCLAMATION No.1048/2017

RAILWAY TRANSPORT ADMINSTRATION PROCLAMATION

WHEREAS,it is necessary to create favorable condition for the expansion of railway transport for making it supportive for the country's social and economic development as a transport sub-sector;

WHEREAS, it is necessary to establish a system that determines national standard for the construction of railway infrastructure and conditions under which railway infrastructure is put in service;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(2) (c) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

SECTION ONE

GENERAL PROVISIONS

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Railway Transport Administration Proclamation No.1048/2017".

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

፪.ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "የእውቅና የምስክር ወረቀት" ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት የተወሰነ አገልግሎት እንዲሰጥ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል እውቅና ለተሰጠው ተቋም የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

፪/ "እውቅና የተሰጠው ተቋም" ማለት የጥገና ተቋም፣ የሥልጠና ማዕከል፣ ወይም የምዘና ተቋም ነው፤

፫/ "ምዘና" ማለት የባቡር ሥራ ባለሙያን ሙያዊ ብቃት ወይም የባቡርንና የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍሎችን የቴክኒክና የደህንነት ብቃትን ለማረጋገጥ ሲባል የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ወይም በምዘና ተቋም የሚከናወን ተግባር ነው፤

፬/ "የምዘና ባለሙያ" ማለት የባቡር ሥራ ባለሞያዎችን፣ ባቡሮችን፣ ወይም የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍልን የቴክኒክና የደህንነት ብቃት ለመመዘን ወይም ለመፈተሸና የሙያ ምስክርነት ለመስጠት እንዲችል የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠው የተፈጥሮ ሰው ነው፤

፭/ "የምዘና ተቋም" ማለት ምዘናን በማከናወን ሙያዊ ምስክርነት እንዲሰጥ በዚህ አዋጅ መሠረት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የእውቅና ምስክር ወረቀት የተሰጠው ተቋም ነው፤

፮/ "ኦዲት" ማለት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የፀደቀ የደህንነት አስተዳዳር ሥርዓት በመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪው ወይም በአገልግሎት ሰጪው ተቋም በአግባቡ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ተብሎ የሚከናወን ተግባር ነው፤

፯/ "የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት

2. **Definitions**

In this Proclamation:

1/ "accreditation certificate" means a certificate given by the body authorized by law to administer railway transport to an accredited institution pursuant to this Proclamation provide a certain service;

2/ "accredited institution" means a maintenance institution, training center, or an assessment institution;

3/ "assessment" means an activity conducted by the body authorized by law to administer railway transport or by an assessment institution to assess professional competency of railway works professionals or technical and safety competency of a train or part of a railway infrastructure;

4/ "assessor" means a natural person given competency license by the body authorized by law to administer railway transport to enable him evaluate or assess technical, safety and functional competence of railway works professionals, trains or railway infrastructure parts;

5/ "assessment institution" means any institution which has an accreditation certificate given by the body authorized by law to administer railway transport in accordance with this Proclamation to give professional testimony after conducting an assessment;

6/ "audit" means an activity carried out with the aim to monitor a safety management system approved by the body authorized by law to administer railway transport is properly implemented by relevant railway infrastructure manager or railway undertaking;

7/ "competency license" means a license issued by the a body authorized by law to administer railway transport to

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ለባቡር ሥራ ባለሙያዎች የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

ፐ/ "የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ሥርዓት" ማለት የኤሌክትሪክ ኃይልን በመጠቀም ለሚንዝ ባቡር የኤሌክትሪክ ኃይል የሚቀርብበት ጠቅላላ ሥርዓት ሲሆን ኤሌክትሪክ የተሸከመ ገመድን፣ የኤሌክትሪክ ኃይል መቀየሪያን ወይም መመጠኛ መሣሪያን፣ የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ ንዑስ ጣቢያን፣ በንዑስ ጣቢያዎች መካከል የተዘረጋ የኤሌክትሪክ መስመርን እና ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መሣሪያዎች ያጠቃልላል፤

8/ "electric power supply system" means an electric system which supplies electric power for an electrified train that includes electric lines, step down or step up or converter systems, electric substations, electric lines connecting substations and related systems and components;

ፑ/ "ፈታኝ" ማለት አሰልጣኝ መሆን አለመሆኑ ከግምት ሳይገባ ሥልጠና ላጠናቀቁ የባቡር ሥራ ባለሙያዎች የንድፈ-ሀሳብና የተግባር ፈተና የሚያዘጋጅ፣ የሚፈትን እና ውጤት የሚሰጥ የተፈጥሮ ሰው ነው፤

9/ "examiner" means a natural person, irrespective of whether he is a trainer or not, who prepare, examine and grade theoretical and practical tests to professionals of railway works who complete relevant trainings;

ፒ/ "የፌደራል ፀጥታ አካላት" ማለት የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን እና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ነው፤

10/ "federal security organs" means the Federal Police Commission and the National Intelligence and Security Service;

፲፩/ "የመሠረተ ልማት አስተዳዳሪ" ማለት የባቡር መሠረተ ልማትን የማስተዳደር በተለይም የመሠረተ-ልማትን የመጠገን፣ በመሠረተ-ልማት ላይ የሚደረግ የባቡር ትራፊክን የመምራት፣ የመቆጣጠርና ተገቢ ምልክቶችንና ማመልከቻዎች የመትከል ኃላፊነት ያለበት ተቋም ነው፤

11/ "infrastructure manager" means an institution which is responsible for administering of a railway infrastructure, particularly for maintaining the railway infrastructure, directing and controlling train traffics, and installing relevant signs and signals along the railway infrastructure;

፲፪/ "ኢንስፔክሽን" ማለት የዚህን አዋጅ እና አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ ሲባል የሚከናወን ተግባር ነው፤

12/ "inspection" means an activity carried out with the aim to ensure proper implementation of this Proclamation; and regulations and directives enacted in accordance with this Proclamation;

፲፫/ "ሎኮሞቲቭ" ማለት ከተገጠመለት ሞተር የሚያገኘውን ኃይል በመጠቀም በሀዲድ ላይ የሚንዝ ማንኛውም ባቡር ነው፤

13/ "locomotive" means any train that moves on a rail using a power generated from a motor mounted on it;

፲፬/ "የጥገና ኃላፊ" ማለት ማንኛውም ጥገና የተደረገለት ባቡር ወይም የመሠረተ-ልማት ክፍል ወይም የእነዚህ አካል የሆነ ማናቸውም መሣሪያ የደህንነት ሥጋት ሳይፈጥር ተመልሶ አገልግሎት ላይ ለመዋል እንደሚችል

14/ "maintenance manager" means a natural person who assures train, parts of railway infrastructure or any equipment which is part of train or railway infrastructure can be put back in operation after maintenance without causing any safety threat;

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

ማረጋገጫ የሚሰጥ የተፈጥሮ ሰው ነው፤

፲፭/ "የጥገና ተቋም" ማለት እንደ አግባብነቱ ባቡርን ወይም የባቡር መሠረተ ልማትን ወይም ሁለቱንም የመጠገን ሥራ እንዲሰራ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የእውቅና የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ተቋም ሲሆን በባቡር መሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ ወይም በአገልግሎት ሰጪ ተቋም ለተመሳሳይ ተግባር የተደራጀ የሥራ ክፍልን ይጨምራል፤

15/ "maintenance institution" means any institution given accreditation certificate by the body authorized by law to administer railway transport to maintain either train or railway infrastructure or both as the case may be; it also includes maintenance departments established under railway infrastructure manager and railway undertakings for the same purpose;

፲፮/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

16/ "Ministry" or "Minister" means the Ministry or Minster of Transport respectively;

፲፯/ "ኔትወርክ" ማለት በአንድ የመሠረተ ልማት አስተዳዳሪ ሀላፊነት ሥር የሚተዳዳር የባቡር መሠረተ-ልማት ነው፤

17/ "network" means a railway infrastructure managed by a single infrastructure manager;

፲፰/ "ሀዲድ" ማለት ባቡር እንዲሔድበት ተብሎ በባቡር መስመር ላይ የተዘረጋ ብረት ነው፤

18/ "rail" means a stretched iron on railway line used for guided movement of train;

፲፱/ "የባቡር መሠረተ ልማት" ማለት የባቡር መስመር፣ የደህንነትና የመገናኛ መሣሪያዎች፣ የጥገና ተቋም፣ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ሥርዓት፣ እና የባቡር ጣቢያዎችን የያዘ መሠረተ ልማት ሲሆን ባቡርን አይጨምርም፤

19/ "railway infrastructure" means an infrastructure which includes railway line, safety and communication equipment, maintenance institution, power supply system, and railway stations, but not includes train;

፳/ "የባቡር መስመር" ማለት ባቡር እንዲሄድበት ተብሎ የተዘረጋን ሀዲድ፣ ሀዲድ የተዘረጋበትን የመሬት ወይም የድልድይ ክፍል፣ ሀዲድን ከሌላ የመንገድ ተጠቃሚ ለመለየት የተሰራ አጥርን ወይም መከለያን እና ከእነዚህ ጋር የተያያዘ መሠረተ-ልማትን አጠቃሎ የሚይዝ የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍል ነው፤

20/ "railway line" means part of a railway infrastructure used for guiding the movement of train and it includes rail, land or bridges on which the rail is stretched, fences and barriers that are built to isolate the rail from other road users and infrastructure linked with them;

፳፩/ "የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት" ማለት ባቡርን በመጠቀም በባቡር መሠረተ ልማት ላይ መንገደኞችን ወይም ዕቃዎችን ከቦታ ወደ ቦታ የማጓጓዝ ተግባር ነው፤

21/ "railway transport service" means an activity of transporting passengers or carrying goods from place to place using train along a rail;

፳፪/ "አገልግሎት ሰጪ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት አግባብነት ያለው ፈቃድ የተሰጠውና ዋነኛ ተግባሩ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት የሆነ

22/ "railway undertaking" means a government or private institution which holds a relevant license in accordance with this Proclamation and whose main function is providing a railway transport service;

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

የመንግስት ወይም የግል ተቋም ነው፤

፳፫/ "የባቡር ሥራ" ማለት በባቡር ማስተርነት፣ በጥገና ኃላፊነት፣ በአሰልጣኝነት፣ በፈታኝነት፣ በባቡር ፍሰት ተቆጣጣሪነት፣ በምዘና ባለሙያነት፣ በደህንነት አስተዳደር ሥርዓት ኃላፊነት የሚከናወን ተግባር ነው፤

23/ "railway work" means activities performed by train master, maintenance manager, trainer, examiner, train dispatcher, assessor, and by a safety management system manager;

፳፬/ "የደህንነትና የመገናኛ መሣሪያዎች" ማለት ደህንነቱ የተጠበቀ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ተብሎ ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም መሣሪያ ማለት ሲሆን የሬዲዮና የምስል መልዕክት መቀበያና ማስተላለፊያ መሣሪያን፣ ከባቡር ውጪ በመሆን የባቡርን እንቅስቃሴ ለማወቅ፣ ለመምራትና ለመቆጣጠር የሚያገለግል የግንኙነትና የመቆጣጠሪያ መሣሪያን፣ በባቡር መሠረተ-ልማት ውስጥና አቅራቢያ የተተከለ ምልክትና ማመላከቻን ይጨምራል፤

24/ "safety and communication equipment" means any equipment used for ensuring safe railway transport service which includes audio and pictorial message transmitting and receiving equipment, equipment that is used to know, guide and control the movement of the train from off board, and signs and signals installed within or beside the railway infrastructure;

፳፭/ "የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ለመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ ደህንነቱ የተረጋገጠ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ዝግጅትና አቅም ያለው መሆኑን ሲረጋገጥ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

25/ "safety authorization" means a license given by the body authorized by law to administer railway transport to the infrastructure manager after its capability and readiness to deliver safe railway transport service is verified in accordance with this Proclamation;

፳፮/ "የደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት" ማለት አገልግሎት ሰጪ ተቋም ደህንነቱ የተረጋገጠ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ዝግጅትና አቅም ያለው መሆኑን ሲረጋገጥ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚሰጥ ምስክር ወረቀት ነው፤

26/ "safety certificate" means a license given by the body authorized by law to administer railway transport to the railway undertaking after its capability to deliver safe railway transport service is verified in accordance with this Proclamation;

፳፯/ "የደህንነት አስተዳደር ሥርዓት" ማለት የመሰረተ ልማት አስተዳዳሪ ወይም የአገልግሎት ሰጪ ተቋም የሚያከናውናቸው ተግባራት ደህንነቱ የተጠበቀ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚዘረጉት ድርጅታዊ መዋቅርና የአሠራር ሥርዓት ነው፤

27/ "safety management system" means a system and organizational structure established by infrastructure manager or railway undertaking to ensure their respective activities are competent enough to provide a safe railway transport services;

፳፰/ "የደህንነት አስተዳደር ሥርዓት ኃላፊ" ማለት የደህንነት አስተዳደር ሥርዓት በአግባቡ ስለመተግበሩ ኃላፊነት

28/ "safety management system manager" means a natural person who is responsible for proper implementation safety management system;

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

ያለበት የተፈጥሮ ሰው ነው፤

፳፱/ "የደህንነት ሥጋት ክስተት" ማለት በባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ የደህንነት ሥጋት የፈጠረ ነገር ግን የባቡር አደጋ ያላስከተለ ማንኛውም ክስተት ወይም ድርጊት ነው፤

29/ "safety threat" means an incident or an act that caused threat but not materialized train accident;

፴/ "ተጨማሪ የባቡር ማስተርነት የምስክር ወረቀት" ማለት የባቡር ማስተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለው ሰው አንድን የባቡር ዓይነት በአንድ የባቡር መስመር ላይ ለመንዳት እንዲችል በዚህ አዋጅ መሰረት በአገልግሎት ሰጪ ተቋም የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

30/ "supplementary train master certificate" means a certificate given by railway undertaking in accordance with this Proclamation to a person holding a train master competency license to enable them to drive a specific train on a specific railway line;

፴፩/ "ባቡር" ማለት የራሱን የሞተር ኃይል በመጠቀም ወይም በሌላ የሞተር ኃይል በተገጠመለት ተሽከርካሪ በመሳብ ወይም በመገፋት በሀዲድ ላይ የሚጓዝ ተሽከርካሪ ሲሆን ሎኮሞቲቭ ወይም ፉርጎ በመባል ይከፈላል፤

31/ "train" means a vehicle which moves on a rail using its own motor or by being pushed or pulled by another motor vehicle which has a power mounted on it, and classified as either locomotive or wagon;

፴፪/ "የባቡር አደጋ" ማለት ከባቡር ትራንስፖርት ጋር በተያያዘ መነሻው ከባቡር መሰረተ ልማት ወይም ከባቡር ውስጥ ሆኖ በባቡር መሰረተ ልማት ውስጥ፣ በባቡር ውስጥ እና ከባቡር መሰረተ ልማት ውጪ ወይም ከባቡር ውጪ በሰው ህይወት ወይም ንብረት ላይ ጉዳት ያስከተለ ድርጊት ወይም አጋጣሚ እና መነሻው ከባቡር መሰረተ ልማት ወይም ከባቡር ውጪ ሆኖ በባቡር እና በባቡር መሰረተ ልማት ውስጥ በሰው ህይወት፣ አካል እና ንብረት ላይ ጉዳትን ያስከተለ ያልተፈለገ ወይም ያልታሰበና ድንገተኛ የሆነ አንድ ክስተት ወይም ተከታታይነት ያላቸው ክስተቶች ነው፡፡

32/ "Train Accident" means unexpected incident or series of incidents that occur initially from the railway infrastructure or in the train causing damage on the life of a person or property in the railway infrastructure or in the train; or outside the the railway infrastructure or the train; and occur outside the railway infrastructure or outside the train causing damage on the life of a person or property inside the train and the railway infrastructure.

፴፫/ "አሰልጣኝ" ማለት ለባቡር ሥራ ባለሙያዎች የንድፈ-ሀሳብ እና የተግባር ትምህርት የሚሰጥ ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ነው፤

33/ "trainer" means any natural person who provides a theoretical and practical training to professionals of railway works;

፴፬/ "የባቡር ፍሰት ተቆጣጣሪ" ማለት በባቡር መሰረተ-ልማት ላይ ባቡሮች የሚያደርጉትን ትራፊክ የሚመራና የሚቆጣጠር የመሰረተ-ልማት አስተዳዳሪ ሠራተኛ የሆነ የተፈጥሮ ሰው ነው፤

34/ "train dispatcher" means a natural person who is employed by infrastructure manager to guide and control the movement of train on the railway infrastructure;

፴፭/ "የሥልጠና ማዕከል" ማለት የባቡር ሥራ ባለሙያዎችን እንዲያሰለጥን የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር

35/ "training center" means any institution accredited by the body authorized by law to administer railway transport to

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል እውቅና የተሰጠው ማንኛውም ተቋም ሲሆን በባቡር መሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ ወይም በአገልግሎት ሰጪ ተቋም ሥር ለተመሳሳይ ተግባር የተደራጀ የሥራ ክፍልን ይጨምራል፤

give training course for railway works' professionals; it also includes training departments established under railway infrastructure manager and railway undertakings for the same purpose;

፴፮/ "የባቡር ማስተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ" ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት መሰረታዊ መስፈርቶችን ላሟላና የብቃት ማረጋገጫ ምዘና ፈተና ላለፈ ሰው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚሰጥ ባቡርን ለመንዳት የሚያስችል ፈቃድ ነው፤

36/ "train master competence license" means a license issued by the body authorized by law to administer railway transport to a person who fulfill basic requirements and passes a competency assessment test in accordance with this Proclamation and qualifies to drive a train;

፴፯/ "የባቡር ማስተር" ማለት በባቡር ውስጥ ሆኖ የባቡሩን እንቅስቃሴ በመምራትና በመቆጣጠር ባቡሩን በሀዲዱ ላይ እንዲንቀሳቀስ የሚያደርግ የተፈጥሮ ሰው ነው፤

37/ "train master" means a natural person guides and controls the movement of train on rail;

፴፰/ "የባቡር ጣቢያ" ማለት ባቡር መንገደኞን ወይም ዕቃን እንዲጭንበትና እንዲያወርድበት ተብሎ በተለይ የተዘጋጀ ስፍራ ሲሆን፤ ተሳፋሪዎች ደህንነታቸው ተጠብቆ ወደ ባቡሩ እንዲገቡና እንዲወጡ ለማድረግ ተብሎ የተዘጋጀ የመሠረተ ልማት ክፍልን፣ የጭነት መጫኛና ማራገፊያ ተርሚናሎችን እና እንደ አግባብነቱ የባቡር እንቅስቃሴ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎችን ይጨምራል፤

38/ "train station" means a special place prepared for trains to embark or disembark passengers and load or unload goods including part of railway infrastructure meant for safe entrance and exist of passengers, loading and unloading terminals and train movement controlling stations, as the case may be;

፴፱/ "አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ" ማለት የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍል፣ ሎኮሞቲቭ፣ ወይም ፉርጎ የተሰራበት ዲዛይን፣ አሰራሩና የቴክኒክ ብቃቱ ደህንነቱ የተረጋገጠ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል መሆኑ ሲረጋገጥ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

39/ "put in service license" means a license issued by the body authorized by law to administer railway transport for a part of railway infrastructure, a locomotive, or a wagon after verifying its design specifications and functional and technical competence are capable to deliver safe railway transport service;

፵/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

40/ "person" means any natural or juridical person;

፵፩/ "ፉርጎ" ማለት መንገደኞችን፣ ዕቃዎችን ወይም እንሰሳትን ለማሳፈር ወይም ለመጫን ተብሎ የተዘጋጀ ሆኖ የራሱ ኃይል የሌለው ባቡር ነው፤

41/ "wagon" means a non-powered train that moves on a rail to transport passengers and carry goods and animals;

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

፵፪/ "የፀና" ማለት የታደሰና ያልታገደ ወይም ያልተሰረዘ ማለት ነው፤

፵፫/ "የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል" ማለት የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ የሚወሰን የመንግስት አስፈፃሚ መስሪያ ቤት ነው፡፡

፵፬/ በዚህ አዋጅ በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ያጠቃልላል፤

፫. የተፈፃሚነት ወሰን

፩/ ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ የባቡር መሠረተ ልማት፣ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚከናወን የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት እና በኢትዮጵያ ውስጥ በሚከናወን የባቡር ሥራ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፤

ሀ)በግል ይዞታነት የተያዘ ሆኖ የመሰረተ ልማት ባለቤቱ የራሱን ጭነት ብቻ ለማጓጓዝ በሚጠቀምበት የባቡር መሠረተ ልማት ላይ፤

ለ) በመዝናኛ ፓርክ ወስጥ ለጨዋታ ወይም ለመዝናኛነት በተገነባ የባቡር መሠረተ ልማት ላይ፤

ሐ) የሀዲድ ስፋቱ ከ ፩፻፴፭ (አንድ ሺ አራት መቶ ሰላሳ አምስት) ሚሊሜትር በታች በሆነ የባቡር ሥራ ወይም የባቡር መሠረተ ልማት ላይ፡፡

፫/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) (ሀ)፣ (ለ)፣ እና (ሐ) የተጠቀሱትን ተግባር ለመቆጣጠር ደንብ ሊወጣ ይችላል፡፡

ክፍል ሁለት

ስለባቡር እና የባቡር መሠረተ ልማቶች

፬. ሎኮሞቲቭ እና ፉርጎዎችን ስለመመዝገብ

፩/ ማናቸውም በኢትዮጵያ ውስጥ አገልግሎት ላይ የሚውሉ ሎኮሞቲቮች እና ፉርጎዎች የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል መመዝገብ እና የምዝገባ ምስክር

42/ "valid" means a renewed and not suspended or revoked.

43/"a body authorized by law to administer railway transport" means the Ministry of Transport or a government executive organ determined by regulation to be issued by Council of Ministers.

44/ any expression in masculine gender includes feminine.

3. Scope of Application

1/ This Proclamation shall apply on railway infrastructure build in Ethiopia, railway transport service provided in Ethiopia and on railway work carried out in Ethiopia.

2/ Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, the provisions of this Proclamation shall not apply on:

a) privately owned railway infrastructure that exists solely for the use by the infrastructure owner for its own freight operation;

b) A railway infrastructure built and operated at an amusement park;

c) A railway work or a railway infrastructure which has a rail gauge less than 1,435 millimeters.

3/ A regulation may be issued, if necessary, to govern the activities mentioned on (a), (b), and (c) of sub-article (2) of this Article.

SECTION TWO

TRAIN AND RAILWAY INFRASTRUCTURE

4. Registration of Locomotives and Wagons

1/ Any locomotive and Wagon put in service in Ethiopia shall be registered by the body authorized by law to administer railway transport and have a registration certificate.

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

ወረቀት ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተመዘገቡ ሎኮሞቲቮች እና ፉርጎዎች የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚሰጥ መለያ ቁጥር ይኖራቸዋል፤ መለያ ቁጥሩም በጉልህ ሊታይ የሚችል ሆኖ በሎኮሞቲቮች እና ፉርጎዎች የፊትና የኋላ እንዲሁም የግራና የቀኝ አካላት ላይ መፃፍ አለበት፡፡

2/ Locomotives and wagons registered in accordance with sub-article (1) of this Article shall have registration number given by the body authorized by law to administer railway transport; and the registration number shall be clearly seen and written in front and behind as well as left and right body part of the locomotive and wagons.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተመዘገበ ሎኮሞቲቭ ወይም ፉርጎ አገልግሎት መስጠት ሲያቆም ምዝገባው ይሰረዛል።

3/ The registration made according to sub-article (1) of this Article shall be cancelled when the locomotive or wagon ceases rendering service.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተመዘገበ ሎኮሞቲቭ ወይም ፉርጎ ባለቤትነት ለሌላ ሰው የተላለፈ እንደሆነ ምዝገባው እንደገና መከናወን አለበት።

4/ Any locomotive or wagon register according to sub-article (1) of this Article if transferred to another person shall be register again.

፭/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተከናወነ የሎኮሞቲቭ ወይም የፉርጎ ምዝገባ መታደስ የማያስፈልገው ነው።

5/ Without prejudice to sub-articles (3) and (4) of this Article, a registration made in accordance with sub-article (1) of this Article does not need renewal.

፭. <u>ምዝገባን ስለሚያስከለክሉ ሁኔታዎች</u>

የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል የኢትዮጵያ ደረጃዎችንና የደህንነት ደንቦችን የማያሟሉ ሎኮሞቲቮች እና ፉርጎዎች እንዳይመዘገቡ ወይም ወደሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ለመከልከል ይችላል።

5. <u>Conditions Barring Registration</u>

The body authorized by law to administer railway transport may bar the registration or importing of locomotives and wagons which does not meet Ethiopian standards and safety Regulations.

፮. <u>ያለፈቃድ ባቡርን እና የባቡር መሠረተ-ልማቶችን አገልግሎት ላይ ማዋል ስለመከልከሉ</u>

6. <u>Prohibition of Putting In-Service of Trains and Railway Infrastructures without License</u>

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠና የፀና አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ ያልተሰጣቸውን ሎኮሞቲቮች፣ ፉርጎዎች ወይም የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍሎችን ተጠቅሞ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት አይችልም፡፡

1/ No person shall provide railway transport service by using any locomotive, wagon or any part of railway infrastructures which do not have a valid put in service license issued in accordance with this Proclamation.

፪/ ማንኛውም ሰው አገልግሎት ላይ ለማዋል ፈቃድ ያገኘባቸውን ሎኮሞቲቮችን፣ ፉርጎዎችን ወይም

2/ No person shall put in service a locomotives, wagons or railway infrastructures for the type of service other than

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

የባቡር መሠረተ-ልማቶችን ፈቃድ ከተሰጠበት የአገልግሎት ዓይነት ውጪ ሊጠቀምባቸው አይችልም፡፡

he has been given a license.

፯. ሎኮሞቲቮችን እና ፉርጎዎችን አገልግሎት ላይ ስለማዋል

፩/ ማንኛውም ሎኮሞቲቭ ወይም የመንገደኛ ማመላለሻ ፉርጎ ለምዝገባ ሲቀርብ፣ ቀጥሎም በየሁለት ዓመቱ የኢትዮጵያን ደረጃዎችንና የደህንነት ደንቦችን የሚያሟላ ስለመሆኑ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የቴክኒክ ፍተሻ እየተደረገበት አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

7. Put In-Service of Locomotives and Wagons

1/ Any locomotive or passengers wagon shall be given put in-service license when they appear for registration and subsequently every two years after verifying fulfillment of the standards and safety regulations of Ethiopia through technical inspection by the body authorized by law to administer railway transport.

፪/ ማንኛውም የእቃ ማጓጓዣ ፉርጎ ለምዝገባ ሲቀርብ፣ ቀጥሎም በየሶስት ዓመቱ የኢትዮጵያን ደረጃዎችንና የደህንነት ደንቦችን የሚያሟላ ስለመሆኑ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የቴክኒክ ፍተሻ እየተደረገበት አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

2/ Any freight wagon shall be given put in-service license when they appear for registration and subsequently every three years after verifying fulfillment of the standards and safety regulations of Ethiopia through technical inspection by the body authorized by law to administer railway transport.

፰. የባቡር መሠረተ-ልማቶችን አገልግሎት ላይ ስለማዋል

8. Put In-Service of Railway Infrastructure

፩/ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍሎች የኢትዮጵያን ደረጃዎችንና የደህንነት ደንቦችን የሚያሟሉ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ ለእያንዳንዱ የመሠረተ-ልማት ክፍል በተናጥል አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ ይሰጣል፡፡

1/ The body authorized by law to administer railway transport shall issue put in service license for each of railway infrastructure parts separately upon ensuring their compliance with Ethiopian standard and safety regulations.

፪/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጥ የባቡር መሠረተ-ልማቶችን አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ ለሙሉ ኔትወርክ ወይም ለኔትወርኩ የተወሰነ ክፍል ሊሰጥ ይችላል፡፡

2/ The put in service license issued in accordance with this Article may be given for the whole or part of the network.

፫/ የባቡር መሠረተ-ልማቶችን አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ በየሶስት ዓመቱ መታደስ ይኖርበታል፡፡

3/ The railway infrastructure put in service license shall be renewed every three years.

፱. ባቡር እና የባቡር መሠረተ-ልማት ግብዓትን

ስለማምረትና ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባት ማንኛውም ሰው በውጪ ሀገር የተመረተ ባቡር እና የባቡር መሠረተ-ልማት ግብዓት ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት፣

9. Producing and Importing of a Train and Railway Infrastructure Component

Any person cannot import or produce in Ethiopia trains and railway infrastructure inputs unless the body authorized by

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

ወይም እነዚህኑ በኢትዮጵያ ውስጥ ለማምረት የሚችለው ሎኮሞቲቮቹ፣ ፉርጎዎቹ ወይም የባቡር መሠረተ-ልማት ማምረቻ ግብአቶቹ አሰራርና ቴክኒክ የኢትዮጵያን የጥራት እና የደህንነት ደረጃ የሚያሟሉ መሆናቸው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

ክፍል ሦስት

ስለባቡር ሥራ ባለሙያዎች

፲. የባቡር ሥራ ባለሙያዎችን ስለመመዝገብ

፩/ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል በባቡር ሥራዎች ላይ የተሰማራን ማንኛውም ሰው የሚመዘገብበት ሀገር አቀፍ የባቡር ሥራ ባለሙያዎች መዝገብ አደራጅቶ ይይዛል።

፪/ ማንኛውም ሰው የባቡር ሥራዎችን ለመስራት የሚችለው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የባቡር ሥራ ባለሙያዎች መዝገብ ላይ የተመዘገበ እንደሆነና እንደ አግባብነቱ በባለሥልጣኑ የተሰጠ የፀና የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለው እንደሆነ ብቻ ነው።

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረግ ምዝገባ ለአምስት ዓመታት ፀንቶ ይቆያል፤ ሆኖም ተመዝጋቢው በአምስት ዓመቱ መጨረሻ ምዝገባውን በማሳደስ ለማራዘም ከፈለገ በ ፴ ቀናት ውስጥ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ማመልከት ይችላል።

፲፩. የባቡር ሥራዎች ለመስራት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የሚያስፈልግ ስለመሆኑ

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠው የጸና የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ከሌለው በስተቀር የባቡር ሥራዎችን ለመስራት አይችልም።

law to administer railway transport ensures the functional and technical specification of locomotives, wagons and railway infrastructure inputs meet the quality and safety standards of Ethiopia.

SECTION THREE

RAILWAY WORKS PROFESSIONALS

10. Registration of Railway Works Professionals

1/ The body authorized by law to administer railway transport shall prepare and maintain railway works professionals national registry book for the registration of any person engaged in railway works.

2/ Any person may engage in railway works if and only if he is registered in the railway works professional registry book in accordance with sub-article (1) of this Article and he has a valid competency license, as appropriate.

3/ Any registration made pursuant to this Article shall remain valid for five years; provided, however, the registered person may apply to the body authorized by law to administer railway transport within 30 days to extend the validity period by renewing it at the end of the five years.

11. Necessity of Competency License for Railway Works Professionals

1/ No person shall perform railway works without a valid competency license issued by the body authorized by law to administer railway transport in accordance with this Proclamation.

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

፪/ ማንኛውም የባቡር ሥራን የሚሰራ ሰው የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በደረጃ ወይም በዓይነት ተለይቶ የተሰጠው እንደሆነ እንደ አግባብነቱ ከተሰጠው ደረጃ ወይም ዓይነት ውጪ የሆኑ የባቡር ሥራዎችን ለመስራት አይችልም፡፡

2/ Any person, who has been issued competence license with specific type and level of engagement, shall not perform those works other than the level or type of the railway works specified on the license, as the case may be.

፫/ ማንኛውም በሕግ ያልተከለከለ ሰው የባቡር ሥራዎችን ለመስራት የሚያስችለው የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዲሰጠው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠውን አካል በጽሁፍ ለመጠየቅ ይችላል፡፡

3/ Any person who is not legally interdicted may apply to the body authorized by law to administer railway transport in writing for competency license to engage in a railway works.

፬/ ተጨማሪ መስፈርቶች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩ (፪) ድንጋጌ መሰረት በመመሪያ የሚወጡ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለባቡር ሥራዎች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት የሚቻለው አመልካቹ የሚከተሉትን መሠረታዊ መስፈርቶች አሟልቶ የሚገኝ ሲሆን ነው፤

4/ Without prejudicing the possibility of additional preconditions may be determined by Directive issued in accordance with Article 51 (2) of this Proclamation competency license for railway works may be issued when the applicant fulfills the following basic requirements:

ሀ) የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለጠየቀበት የባቡር ሥራ በታወቀ ተቋም ተገቢውን ሥልጠና ወስዶ በብቃት ያጠናቀቀ ስለመሆኑ ማስረጃ ካቀረበ፤

a) produces evidence showing that he has successfully completed, from an accredited training institute, the training required for the railway work he is applying for;

ለ) አግባብነት ያለውን የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ምዘና ፈተናን ያለፈ እንደሆነ፤

b) passes the competence assessment test given by the body authorized by law to administer railway transport as the case may be;

ሐ) ዕድሜው ፲፰ ዓመትና ከዚያ በላይ ከሆነ፤

c) age 18 years and above;

መ) የባቡር ሥራውን ለመስራት የሚያስችል የተሟላ የአካልና የአዕምሮ ጤንነት ያለው ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የህኪም ማስረጃ ካቀረበ፤

d) produces medical evidence showing that he is physically and mentally fit to perform railway work;

ሰ) ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ ከሆነ የባቡር ሥራን እንዲሰራ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠ ማስረጃ ካቀረበ፤

e) if he is an Ethiopian national, evidence showing that he has been permitted by the body authorized by law to administer railway transport to perform railway work;

ረ) ኢትዮጵያዊ ዜግነት የሌለው ከሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ እንዲሰራ ከሚመለከተው አካል የሥራ ፈቃድ የተሰጠው እና የባቡር ሥራን

f) If he is not Ethiopian national, evidence of work permit issued by appropriate organ to work in Ethiopia and permit from the body authorized by law

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሰራ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠ ማስረጃ ካቀረበ፤

to administer railway transport to perform railway work in Ethiopian.

፭/ ማንኛውም የባቡር ሥራ ባለሙያነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለሦስት ዓመታት ጸንቶ የሚቆይ ይሆናል፤ ሦስተኛው ዓመት እንደተጠናቀቀ ቀጥሎ ባሉት ፴ ቀናት ውስጥ መታደስ አለበት፡፡

5/ Any railway work competency license shall be valid for three years; and be renewed within 30 days after the laps of three years.

፮/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) ድንጋጌ ቢኖርም የባቡር ማስተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ዕድሜው ሀምሳ ዓመትና በላይ ከሆነ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

6/ Without prejudice to sub-article (5) of this Article, the competency license shall be renewed every year if the train masters is fifty years old or above.

፲፪. **<u>ባቡርን ስለመንዳት</u>**

ማንኛውም ሰው ባቡርን ለመንዳት የሚችለው፤

12. <u>Train Driving</u>

Any person may drive a train if and only if he has:

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ መሠረት የተሰጠና የፀና የባቡር ማስተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለው የሆነ እንደሆነ፤ እና

1/ a valid train master competency license issued pursuant to Article 11 of this Proclamation; and

፪/ አግባብነት ያለው ተጨማሪ የባቡር ማስተርነት ምስክር ወረቀት ያለው እንደሆነ፤

ብቻ ነው፡፡

2/ a relevant supplementary train master certificate.

፲፫. **<u>ስለ ተጨማሪ የባቡር ማስተርነት ምስክር ወረቀት</u>**

13. <u>Supplementary Train Master Certificate</u>

፩/ ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የባቡር ማስተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠውን ሰው ማንኛውንም ዓይነት ባቡር እንዲነዳ ከማድረጉ በፊት የባቡሩን ዓይነት እና ባቡሩ የሚነዳበትን መስመር የተመለከተ ተጨማሪ ሥልጠና እንዲወስድና ብቃቱ እንዲረጋገጥ ማድረግ አለበት፡፡

1/ Any railway undertaking shall provide supplementary training and verify competence of a person who has a train master competency license given by the body authorized by law to administer railway transport concerning type of train and railway line on which the train master may drive.

፪/ አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰውን ሥልጠና የሚሰጥበትንና ምዘና የሚከናወንበትን ሥርዓት በደህንነት አስተዳደር ሥርዓቱ ውስጥ በማካተት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን

2/ A railway undertaking shall include in its safety management system its system established for providing supplementary trainings and making assessments in accordance with sub-article(1) of this Article; and shall obtain approval for same from the body authorized by

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

ለተሰጠው አካል ማቅረብና ማፀደቅ አለበት፡፡

፫/ አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ብቃቱን ላረጋገጠው የባቡር ማስተር ተጨማሪ የባቡር ማስተርነት የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት፤ የምስክር ወረቀቱ የባቡር ማስተሩ ለመንዳት የሚችለውን የባቡር ዓይነትና ባቡሩን ሊነዳበት የሚችልበትን የባቡር መስመር የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

3/ A railway undertaking shall issue supplementary train master certificate for a person whose competence is verified as per sub-article (1) of this Article; and the certificate shall specify the type of train and railway line on which the train master may drive.

ክፍል አራት

ስለደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ፤ ምስክር ወረቀት፣ እና ስለታሪፍ

SECTION FOUR

SAFETY AUTHORIZATION, SAFETY CERTIFICATE AND TARIFF

፲፬. ለባቡር መሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ ስለሚሰጥ የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ

፩/ ማንኛውም ሰው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠና የፀና የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ሳይኖረው የራሱን ወይም በይዞታው ያለን ማንኛውንም የባቡር መሠረተ ልማት አገልግሎት ላይ እንዲውል ለማድረግ አይችልም፡፡

፪/ ማንኛውም በሕግ ያልተከለከለ ሰው የራሱ ወይም በሕግ መሰረት በይዞታው ያደረገውን የባቡር መሠረተ ልማት አገልግሎት ላይ ለማዋል የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዲሰጠው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ማመልከት ይችላል፡፡

፫/ የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተዘጋጀውን ፎርም በመሙላት ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፤

ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ በባቡር መሠረተ-ልማት አስተዳዳሪነት ለመስራት እንዲችል በሚኒስቴሩ የተመዘገበበትን የምዝገባ የምስክር ወረቀት፤

ለ) የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ

14. Safety Authorization Issued for an Infrastructure Manager

1/ No person may put a railway infrastructure owned by him or under his possession in service unless he has a valid safety authorization issued by the body authorized by law to administer railway transport.

2/ Any person who is not legally interdicted may apply to the body authorized by law to administer railway transport to get safety authorization to put in service infrastructure owned by him or under his possession.

3/ The application for safety authorization request shall be submitted by filling the form prepare by the body authorized by law to administer railway transport and accompanied by the following documents:

a) a registration certificate for working as railway infrastructure manager in Ethiopia;

b) railway infrastructure safety management system

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

ሥልጣን በተሰጠው አካል የጸደቀ የባቡር መሠረተ-ልማት የደህንነት አስተዳደር ሥርዓት ሰነድ፤

ሐ) ለቀጠራቸው የባቡር ሥራ ባለሙያዎች የፀና የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድና የቅጥር ማስረጃዎች፤

መ) የባቡር መሠረተ ልማቱን ለመጠገን ላደራጀው የሥራ ክፍል የተሰጠውን የዕውቅና ምስክር ወረቀት፤

ሰ) ለባቡር መሠረተ ልማት ክፍሎች የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠ አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ፤

ረ) የባቡር መሠረተ ልማቱ ለአገልግሎት የሚውልበትን ዝርዝር መረጃ የያዘ ሰነድ፤

ሠ) በባቡር መሠረተ-ልማቱ አማካኝነት ሊደርስ ለሚችል ጉዳት የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ የገባ መሆኑን የሚሳይ ማስረጃ::

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (መ) የተደነገገው ቢኖርም የባቡር መሠረተ-ልማቶቹ የሚጠገኑት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የእውቅና የምስክር ወረቀት በተሰጠው ሌላ የጥገና ተቋም አማካኝነት የሆነ እንደሆነ የመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪው ለጥገና የሥራ ክፍሉ የዕውቅና የምስክር ወረቀት ማቅረብ አያስፈልገውም፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጠው የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ የመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪው ለሚያስተዳደረው ኔትዎርክ በሙሉ ወይም ለኔትዎርኩ ከፊል ክፍል ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡

፮/ የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ በየሁለት ዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

approved by the body authorized by law to administer railway transport;

c) a valid competency license and evidence of employment for railway work professionals it hired;

d) accreditation certificate issued for the department it organized to maintain the railway infrastructure;

e) put in service license issued by the body authorized by law to administer railway transport for railway infrastructure parts;

f) a document showing details of putting the infrastructure in service;

g) Evidence showing third party insurance coverage for damage that may be sustained by the railway infrastructure.

4/ Notwithstanding the provision of sub-article (3) (d) of this Article, if the railway infrastructure is maintained by another maintenance institute issued accreditation certificate by the body authorized by law to administer railway transport, the infrastructure manager shall not be required to provide accreditation certificate for its maintenance work department.

5/ Safety authorization may be issued for the whole or part of the network administered by the infrastructure manager.

6/ Infrastructure manager safety authorization shall be renewed every two years.

፲፭. **ለአገልግሎት ሰጪ ተቋም ስለሚሰጥ የደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት**

፩ ማንኛውም ሰው የባቡር ትራንስፖርትን

15. Safety Certificate Issued for Railway Undertaking

1/ Any person shall not give a railway transport service

0915735560

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠ የፀና የደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳይኖረው የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት አይችልም፡፡

unless he has a valid safety certificate issued by the body authorized by law to administer railway transport.

፪/ በሌላ ሕግ የተከለከለ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው የራሱን ወይም የሌላን ሰው የባቡር መሠረተ-ልማት ተጠቅሞ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪነት ሥራን ለመስራት እንዲችል የደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠውን አካል ለመጠየቅ ይችላል፡፡

2/ Any person who is not legally interdicted may apply to the body authorized by law to administer railway transport to get safety certificate to provide a railway transport service using his own railway infrastructure or an infrastructure owned by another person.

፫/ የደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተዘጋጀውን ፎርም በመሙላት ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፤

3/ An application for safety certificate shall be submitted by filling the form prepare by the body authorized by law to administer railway transport and accompanied by the following documents:

ሀ) በዚህ አዋጅ መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ በአገልግሎት ሰጭነት ለመስራት በሚኒስቴሩ የተመዘገበበት የምዝገባ ምስክር ወረቀት፤

a) registration certificate issued by the Ministry pursuant to this Proclamation to engage as railway undertaking in Ethiopia;

ለ) የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የጸደቀ የአገልግሎት ሰጪ ተቋም የደህንነት አስተዳደር ሥርዓት ሰነድ፤

b) railway undertakings' safety management system documents approved by the body authorized by law to administer railway transport;

ሐ) በዚህ አዋጅ መሠረት ለፉርጎዎቹ፣ ለሎኮሞቲቮቹ፣ እና ለባቡር ጥገና የሥራ ክፍል የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠ የፀና አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ፤

c) a valid put in service license issued by the body authorized by law to administer railway transport pursuant to this Proclamation for its wagons, locomotives and maintenance department;

መ) ባቡሮችን ለመጠገን ተግባር ላደራጀው የሥራ ክፍል የተሰጠውን የዕውቅና ምስክር ወረቀት፤

d) accreditation certificate issued for the department it organized to maintain trains;

ሰ) ለቀጠራቸው የባቡር ሥራ ባለሙያዎች በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠና የፀና የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድና የቅጥር ማስረጃ፤

e) a valid competency license issued pursuant to this Proclamation and evidence of employment for railway work professionals it hired;

ረ) በባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት

f) Evidence showing third party insurance coverage for

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

ለሚደርስ ጉዳት የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ የተገባበት ማስረጃ፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (መ) የተደነገገው ቢኖርም ባቡሮቹ የሚጠገኑት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የእውቅና ምስክር ወረቀት በተሰጠው የጥገና ተቋም አማካኝነት የሆነ እንደሆነ አገልግሎት ሰጭ ተቋሙ ለራሱ የጥገና ሥራ ክፍል የዕውቅና ምስክር ወረቀት ማቅረብ አያስፈልገውም፡፡

፭/ የደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

damage that may be sustained during railway transport service.

4/ Notwithstanding the provision of sub-article (3) (d) of this Article, if the trains are maintained by another maintenance institute given accreditation certificate by the body authorized by law to administer railway transport, the railway undertaking shall not provide accreditation certificate for its maintenance work department.

5/ A safety certificate shall be renewed every year.

፲፮. **ስለታሪፍ**

፩/ ማንኛውም የመሠረተ ልማት አስተዳዳሪ ለሚሰጠው የባቡር መሠረተ ልማት የመጠቀም አገልግሎት የሚያስከፍለውን የክፍያ መጠንና አገልግሎቱ የሚሰጥባቸውን ሁኔታዎች ለሚኒስቴሩ አቅርቦ ሳያጸድቅ ተግባራዊ ማድረግ አይችልም፡፡

፪/ ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ ተቋም ለሚሰጠው የመንገደኛና የዕቃ ማጓጓዝ አገልግሎት የሚያስከፍለውን የክፍያ መጠንና አገልግሎቱ የሚሰጥባቸውን ሁኔታዎች የያዘ በሚኒስቴሩ የፀደቀ ወቅታዊ ታሪፍ ከሌለው በስተቀር የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎትን በክፍያ ለመስጠት አይችልም፡፡

፫/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) አፈፃፀም ማንኛውም የመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪና አገልግሎት ሰጭ ተቋም ለሚሰጠው አገልግሎት ሊያስከፍል የሚፈልገውን የታሪፍ መጠን ለመወሰን የተጠቀመባቸውን ዝርዝር መረጃዎች በማያያዝ ሚኒስቴሩ በሚወስነው ፎርም መሠረት ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት፡፡

፬/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ታሪፍ እንዲፀድቅ ጥያቄ ሲቀርብለት፣ ታሪፉን ለመወሰን ጥቅም ላይ የዋሉትን መረጃዎች እንዲሁም

16. Tariff

1/ No infrastructure manager shall apply tariff and condition for the infrastructure service which it allows to be used without submitting and getting approval from the Ministry.

2/ No railway undertaking shall give railway transport service through payment unless it has an updated tariff, approved by the Ministry, that specify the payment it charges and conditions on which it gives the service of transporting passengers and goods.

3/ For the application of sub-article (1) and (2) of this Article, any infrastructure manager and railway undertaking shall submit to the Ministry, payment it intends to charge for service it provides, and detailed description of method it uses to fix the tariff, by using a form that may be decided by the Ministry.

4/ The Ministry upon receiving a request for approval of the tariff in accordance with sub–article (3) of this Article may approve or amend the tariff after evaluating

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች በመመርመር ለማጽደቅ ወይም አሻሽሎ ለመወሰን ይችላል፡፡

ክፍል አምስት
ስለሥልጠና፣ ጥገና፣ እና ምዘና

፲፯. የእውቅና ምስክር ወረቀት አስፈላጊነት

የሚከተሉትን ተግባራት ለማከናወን የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠና የፀና የእውቅና ምስክር ወረቀት መኖር አለበት፤

፩/ የባቡር ሥራ ባለሙያዎችን ለማሠልጠን፤

፪/ ባቡርን እና የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍሎችን ለመጠገን፤

፫/ የባቡር ሥራ ባለሙያዎችን የብቃት ደረጃ ለመመዘን እና የባቡርንና የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍሎችን የቴክኒክና የደህንነት ብቃት በመፈተሽ የሙያ ምስክርነት ለመስጠት፡፡

፲፰. የባቡር ሥራ ባለሙያዎችን ስለማሰልጠን

፩/ ማንኛውም ተቋም፣ የመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም የባቡር ሥራ ባለሙያዎችን ለማሰልጠን የሚችለው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ (፩) መሰረት የተሰጠ የፀና የእውቅና ምስክር ወረቀት ያለው እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

፪/ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚሰጥ የእውቅና ምስክር ወረቀት የሥልጠና ማዕከሉ ሥልጠና እንዲሰጥ የተፈቀደለትን የባቡር ሥራ ዓይነቶችንና የሚሰጠውን የሥልጠና ደረጃ የሚገልፅ መሆን አለበት፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ቢኖሩም አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት እውቅና የተሰጣቸው ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የባቡር ሥራ ባለሞያዎችን በመጀመሪያ ድግሪና ከዚያ በላይ በሆነ ደረጃ ለማስተማር የባቡር ትራንስፖርትን

the information used to decide the tariff as well as other relevant information.

SECTION FIVE
TRAINING, MAINTENANCE AND ASSESSMENT

17. Necessity of Accreditation Certificate

There shall be a valid accreditation certificate issued by the body authorized by law to administer railway transport to perform the following activities:

1/ to train railway work professionals;

2/ to maintain train and railway infrastructure parts;

3/ to give professional witness upon assessment of competence of railway operational work professionals and assessment of technical and safety capacity of trains and railway infrastructure parts.

18. Training of Railway Works' Professionals

1/ Any institute, infrastructure manager or railway undertaking may provide training for railway work professionals only if it has a valid accreditation certificate issued as per Article 17 (1) of this Proclamation.

2/ The accreditation certificate issued by the body authorized by law to administer railway transport shall specify the type of railway works and level of the training provided by the training center.

3/ Notwithstanding the provision of this Article, higher education institutions accredited by appropriate law to provide first degree and above, for railway works' professionals, shall not be subject to accreditation

0915735560

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የእውቅና ምስክር ወረቀት ማግኘት አያስፈልጋቸውም።

፲፱. ስለሥልጠና ማስረጃ እና የብቃት ማረጋገጫ ምዘና

፩/ የማንኛውም የባቡር ሥራ ባለሞያ የሚያቀርበው የሥልጠና ማስረጃ ተቀባይነት የሚኖረው ሥልጠናውን የወሰደው የእውቅና ምስክር ወረቀት በተሰጠው የሥልጠና ማዕከል ከሆነ ብቻ ነው።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ተቀባይነት ያለው የስልጠና ማስረጃ ማቅረብ የቻለ ማንኛውም ሰው ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሰረት በሚወጣ መመሪያ በውጪ ሀገር ከሚገኝ የስልጠና ማዕከል ያገኘው የስልጠና ማስረጃ ተቀባይነት ያገኘለት ማንኛውም ሰው በባቡር ሥራ ባለሙያነት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ከመመዝገቡ በፊት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ ፬ ፊደል ተራ (ለ) መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ምዘና መውሰድና የማለፊያ ነጥብ ማምጣት አለበት።

፳. ባቡርን እና የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍሎችን ስለመጠገን

፩/ ማንኛውም ተቋም፣ የመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም ባቡርን ወይም የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍሎችን ለመጠገን የሚችለው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ (፪) መሠረት የተሰጠና የፀና የእውቅና ምስክር ወረቀት ያለው እንደሆነ ብቻ ነው።

፪/ ማንኛውም የመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠ አግባብነት ያለው የእውቅና ምስክር ወረቀት ባለው የጥገና ተቋም ካልሆነ በስተቀር በሌላ በማናቸውም ተቋም ወይም ሰው የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍልን ወይም ባቡርን እንዲጠገን ለማድረግ

certificate issued by the body authorized by law to administer railway transport.

19. Training Qualification Document and Competency Assessment

1/ Training qualification document submitted by any railway work's professional shall be accepted only if the training is given by an accredited training institute.

2/ Any person who submit acceptable training qualification document as per sub-article (1) of this Article or any person whose training qualification document obtained from a foreign training institution is accepted as per directive issued pursuant to sub-article (2) of Article 51 of this Proclamation shall take a competency assessment test and score a passing mark pursuant to paragraph (b) of sub-article (5) of Article 11 of this Proclamation, prior to registering as a railway operational work professional by the body authorized by law to administer railway transport.

20. Maintenance of Train and Railway Infrastructure Parts

1/ Any institute, infrastructure manager or railway undertaking may provide maintenance service for train or railway infrastructure parts if and only if it has a valid accreditation certificate issued as per of Article 17 (2) of this Proclamation.

2/ No infrastructure manager or railway undertaking can make its infrastructure parts or trains maintained by any other maintenance institution or person, except with those having valid accreditation certificate issued by the body authorized by law to administer railway transport.

0915735560

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

አይችልም፡፡

፫/ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚሰጠው የእውቅና ምስክር ወረቀት የጥገና ተቋሙ ሊጠግናቸው የሚችላቸውን የባቡር ዓይነቶች፣ የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍሎችን እና ሊያከናውነው የሚችለውን የጥገና ደረጃ የሚገልፅ መሆን አለበት፡፡

3/ The accreditation certificate issued by the body authorized by law to administer railway transport shall specify the type of train, railway infrastructure parts to be maintained and level of maintenance to be provided by the maintenance institute.

፳፩. <u>የባቡር ሥራ ባለሙያዎችን ስለመመዘን</u>

21. <u>Assessment of Railway Works' Professionals</u>

፩/ የባቡር ሥራ ባለሙያዎች የብቃት ደረጃ ምዘና የሚከናወነው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ነው፡፡

1/ The body authorized by law to administer railway transport shall be assessor of the competency level of railway work professionals.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል የብቃት ማረጋገጫ ምዘናው በሌላ የትምህርትና ስልጠና ተቋም፣ የስልጠና ማዕከል ወይም በሌላ ማናቸውም ተቋም እንዲያከናወን ለማድረግ ይችላል፡፡

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the body authorized by law to administer railway transport may decide the assessment of competency level of railway work's professionals to be performed by other educational and training institutions; training center or any other institution.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በሕግ አግባብ የተቋቋመ የትምህርት ወይም የስልጠና ማዕከል ወይም ሌላ ማናቸውም ተቋም አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የባቡር ሥራዎችን ለመመዘን እንዲችል እውቅና እንዲሰጠው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠውን አካል ለመጠየቅ ይችላል፤ ሆኖም ማንኛውም የሥልጠና ማዕከል ራሱ ያሰለጠናቸውን የባቡር ሥራ ባለሙያዎች መመዘን የተከለከለ ሲሆን፣ ለሌላ ፈቃድ የተሰጠው አካል በማቅረብ እና ማስመዘን አለበት፡፡

3/ Without prejudice the provision of sub-article (2) of this Article, any educational or training institution or any other institution established in accordance with law may request the body authorized by law to administer railway transport to obtain accreditation certificate to assess one or more than one railway works professionals; provided, however, that it is prohibited for any training institution to assess its own trainees and it shall present its trainees to other licensed institutions for assessment.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ምዘናውን በአግባቡ አላከናወነም ለማለት የሚያበቃ ምክንያት ሲኖረው የባቡር ሥራ ባለሙያውን በራሱ ባለሙያዎች

4/ Notwithstanding the provisions of sub-article (2) of this Article, if the body authorized by law to administer railway transport has sufficient reason to conclude that the assessment is not made properly, it may decide to re-assess the railway work's professionals by its own assessment professionals or by other assessment

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

ሊመዝነው ወይም በሌላ የምዘና ተቋም በድጋሚ እንዲመዘን ለማድረግ ይችላል፡፡

፳፪. <u>ባቡርን እና የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍሎችን የደህንነት ብቃት ስለመመዘን</u>

፩/ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ባቡርን ወይም አንድ ወይም ከአንድ በላይ የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍልን የቴክኒክና የደህንነት ብቃት ደረጃ ላይ ፍተሻ በማድረግ ሙያዊ ምስክርነት ለሚሰጡ የምዘና ተቋማት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት የእውቅና ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

፪/ ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም፣ የመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋም፣ የባቡር ወይም የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍሎች አምራች ተቋም፣ ወይም ሌላ ማናቸውም ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተገለፀውን ተግባር ለመፈፀም የእውቅና ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ማመልከት ይችላል፡፡

፳፫. <u>የእውቅና ምስክር ወረቀትን ስለማደስ፣ ስለማገድና ስለመሰረዝ</u>

፩/ በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት የሚሰጥ የእውቅና ምስክር ወረቀት በየሶስት ዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም የእውቅና ምስክር ወረቀት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰኑት ምክንያቶች ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡

፳፬. <u>የመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪን እና አገልግሎት ሰጪ ተቋምን ስለመመዘን</u>

፩/ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድን ወይም የደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትን ከመስጠቱ ወይም የሰጠውን ከማደሱ በፊት በዚህ አዋጅና አዋጁን ተከትለው በወጡት ደንቦችና

institution.

22. <u>Safety Competency Assessment for Trains and Railway Infrastructures</u>

1/ The body authorized by law to administer railway transport shall issue accreditation certificate as per sub-article (3) of Article 17 of this Proclamation to assessment institutes which provide professional witness up on assessment of technical and safety capacity level of trains or one or more than one railway infrastructure parts.

2/ Any higher educational institution, infrastructure manager, railway undertaking, trains or railway infrastructure components manufacturer or any other institute may apply to the body authorized by law to administer railway transport for accreditation certificate to perform the activity specified under sub-article (1) of this Article.

23. <u>Renewal, Suspension and Cancellation of Accreditation Certificate</u>

1/ Accreditation certificates issued pursuant to the provisions of this Part shall be renewed every three years.

2/ Any Accreditation certificate may be suspended or canceled by those reasons determined by a Directive issued by the Ministry.

24. <u>Assessment of Railway Undertakings and Infrastructure Managers</u>

1/ The body authorized by law to administer railway transport before issuing or renewing safety authorization or safety certificate may order the infrastructure manager or railway undertaking, to furnish a report prepared by an institute of its own choice about the fulfillment of requirements provided in this Proclamation or

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

መመሪያዎች የተደነገጉ መስፈርቶችና ቅድመ-ሁኔታዎች የተሟሉ ስለመሆናቸው በመረጠው ሌላ ተቋም አስመዝነው የፍተሻውን ሪፖርት እንዲያቀርቡለት የመሰረተ ልማት አስተዳደሪን ወይም አገልግሎት ሰጪን ለማዘዝ ይችላል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል በማናቸውም ጊዜ በራሱ ባለሙያዎች ወይም በመረጠው ሌላ ማናቸውም ሰው አማካኝነት የባቡር መሰረተ ልማት አስተዳደሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ላይ የራሱን ምዘና ከማድረግ አይከለክለውም፡፡

regulations and directives issued pursuant to this Proclamation.

2/ The provision of sub-article (1) of this Article shall not prohibit the body authorized by law to administer railway transport from assessing the infrastructure manager or railway undertaking by its own experts.

ክፍል ስድስት

የደህንነት አስተዳደር ሥርዓት፣ የደህንነት ደረጃዎች እና ሥርዓቶች

SECTION SIX

SAFETY MANAGEMENT SYSTEM AND SAFETY STANDARDS AND SYSTEM

፳፭. የደህንነት አስተዳደር ሥርዓት አስፈላጊነት

፩/ ማንኛውም የባቡር መሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም በየጊዜው ወቅታዊ የሚደረግ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የጸደቀ የደህንነት አስተዳደር ሥርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡

፪/ ማንኛውም የባቡር መሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም እንደአግባብነቱ የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም የደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ወይም እንዲታደስለት በሚጠይቅበት ጊዜ ሁሉ የደህንነት አስተዳደር ሥርዓቱን የሚያሳይ ሰነድ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

25. Importance of Safety Management System

1/ Any infrastructure manager or railway undertaking shall have an updated safety management system approved by the body authorized by law to administer railway transport.

2/ Any infrastructure manager or railway undertaking when requesting for issuance or renewal of safety authorization or competency certificate, as the case may be, shall submit a document showing its safety management system.

፳፮.የደህንነት አስተዳደር ሥርዓት ይዘትና ፎርም

፩/ ተጨማሪ መስፈርቶች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩ (፪) ድንጋጌ መሰረት በመመሪያ የሚወጡ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በባቡር መሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ ወይም በአገልግሎት ሰጪ ተቋም ተዘጋጅቶ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን

26. Content and Form of Safety Management System

1/ Without prejudicing the possibility of additional preconditions may be determined by Directive issued in accordance to sub-article (2) of Article 51 of this Proclamation, a safety management system submitted to the body authorized by law to administer railway transport by the infrastructure manager or railway

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

ለተሰጠው አካል የሚቀርብ የደህንነት አስተዳደር ሥርዓት የሚከተሉትን ዝርዝሮች መያዝ አለበት፤

ሀ) የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎትን አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ሁኔታዎችን የተመለከተ የደህንነት ሥጋት ትንተና፤

ለ) የደህንነት ሥጋቶችን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚከናወኑ ተግባራት፣ የአሰራር ደንቦች፣ ቅደም ተከተሎች እና ተግባራቱን የማከናወን ሥልጣንና ኃላፊነት፤

ሐ) የደህንነት ሥጋት ክስተት ሲከሰት ወይም የባቡር አደጋ ሲያጋጥም ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች፤

መ) የደህንነት ሥጋት ክስተት ሲፈጠር ወይም የባቡር አደጋ በደረሰ ጊዜ የሚሰጠውን ምላሽ፣ የሚከናወኑ ተግባራትንና አፈፃፀሙ የሚመራበት የአሰራር ሥርዓት፤

ሰ) የባቡር ሥራ ባለሙያዎች የደህንነት ሥጋትን ወይም የባቡር አደጋን አስቀድሞ ለመከላከል ሊፈጽሟቸው የሚገቡ የጥንቃቄ ተግባራትና ኃላፊነቶች፤ እንዲሁም የደህንነት ሥጋት ወይም የባቡር አደጋ በደረሰ ጊዜ ሊፈጽሟቸው የሚገቡ ተግባራትና የሚኖርባቸውን ኃላፊነቶች፤

ረ) የደህንነት ግቦችን፣ ስታንዳርዶችን እና የአፈጻጸም ዒላማዎችን ፤

ሠ) ክትትልና ምዘና የሚከናወንበት አግባብና የአሰራር ሂደት፤

ሸ) የባቡር ሥራ ባለሙያዎች ብቃት የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት፤

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የባቡር መሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ በሕግ ሥልጣን ከተሰጣቸው የሕግ አስከባሪና የፀጥታ አካላት የሚሰጡትን የደህንነት ሥጋትን እና የባቡር አደጋን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክሮችን ተቀብሎ በደህንነት አስተዳደር

undertaking shall contain the following details:

a) safety threat analysis concerning conditions that endanger railway transport service;

b) measures taken to avoid or minimize safety threat; work rules, procedures, duties and responsibilities to perform such activities;

c) measures to be taken when safety threat or train accident occurs;

d) actions to be taken, activities to be performed and procedures to be followed when safety threat or train accident occurs;

e) precautionary activities and responsibilities to be performed by a railway work's professionals to prevent safety threat or an accident in advance; as well as the activities and responsibilities to be performed by these professionals when a safety threat or train accident occurs;

f) safety goals, standards and performance objectives;

g) ways and procedures of performing follow up and assessment;

h) Work procedures for assuring competence of railway work's professionals.

2/ Without prejudice to the provision of sub-articles (1) of this Article, any infrastructure manager or railway undertaking shall accept advices, given by law enforcement and security agencies authorized by law, in order to prevent safety threat and train accident; and implement same by incorporating in its safety management systems.

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

ሥርዓቱ ውስጥ ማካተትና መተግበር አለበት፡፡

፳፯. <u>የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎትን ደህንነት ስጋት ላይ የሚጥሉ ስራዎች</u>

የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ደህንነትን ስጋት ላይ ሊጥሉ የሚችሉ በባቡር መሰረተ-ልማቶች አቅራቢያ የሚከናወኑ ማናቸውም የልማትና የግንባታ ስራዎች አስቀድመው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ፈቃድ ማግኘት አለባቸው፡፡

27. <u>Activities that endanger the Safety of Railway Transport Service</u>

Constructions and development activities undertaken around railway infrastructures that may endanger the safety of railway transport service shall obtain prior permission from the body authorized by law to administer railway transport.

ክፍል ሰባት

ስለኦዲትና ኢንስፔክሽን

SECTION SEVEN

AUDIT AND INSPECTION

፳፰. <u>ኦዲትና ኢንስፔክሽን የሚከናወንበት ዓላማ</u>

የባቡር ትራንስፖርት ኦዲትና ኢንስፔክሽን የሚደረግበት ዓላማ በሥራ ላይ የሚገኙ ሎኮሞቲቮች፣ ፉርጎዎች፣ የባቡር መሠረተ ልማቶች፣ የደህንነት አስተዳደር ሥርዓቶች፣ እንዲሁም በባቡር ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች በሕግ የተደነገገውን የደህንነት መስፈርቶች እና ሌሎች ግዴታዎች ያሟሉና የብቃት ደረጃቸው የተረጋገጠ መሆኑን ለማረጋገጥና ለመቆጣጠር፣ ጉድለት ሲገኝም ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ ይሆናል፡፡

28. <u>Purpose of Audit and Inspection</u>

The purpose of railway transport audit and inspection shall be to ensure the competence of persons engaged in railway works as well as ensuring the capacity and standards of locomotives, wagons, railway infrastructures and safety management systems in operation against the requirements prescribed by law; and to take corrective measures on defects, if any.

፳፱. <u>የኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን</u>

፩/ የኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ዋና ዳይሬክተር የሚመደብ ይሆናል፡፡

፪/ የኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ሁሉ በዋና ዳይሬክተሩ የተፈረመ የመታወቂያ ወረቀት መያዝና አግባብነት ባለው ሰው ሲጠየቅ ማሳየት አለበት፡፡

29. <u>Audit and Inspection Officer</u>

1/ The audit and inspection officer shall be assigned by the Director General of the body authorized by law to administer railway transport.

2/ While on duty, the audit and inspection officer shall hold his identification card signed by the Director General and shall show it to a relevant person upon request.

፴. <u>የኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን ሥልጣንና ኃላፊነት</u>

፩/ ማንኛውም የኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን አስቀድሞ ማሳወቅ ሳያስፈልገው በማንኛውም ጊዜ ወደ ባቡር መሠረተ ልማቶች፣ ባቡሮች፣ እና እውቅና የተሰጣቸው ተቋማት ውስጥ በመግባት ይህ አዋጅና

30. <u>Duty and Responsibility of Audit and Inspection Officer</u>

1/ Any audit and inspection officer, at any time, without giving prior notice, may enter in to a railway infrastructure, train, and accredited institute; and perform audit and inspection works to check the proper

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡት ደንቦችና መመሪያዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የኦዲትና ኢንስፔክሽን ሥራ ለማከናወን ይችላል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን አስቀድሞ ማሳወቅ ሳያስፈልገው ወደማንኛውም ባቡርና የባቡር መሰረተ-ልማት ክፍል በመግባት፤

ሀ) የመሰረተ-ልማት አስተዳዳሪው የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት ያቀረበው መረጃ ትክክለኛ ስለመሆኑ እና ይህንኑ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች ተሟልተው የቀጠሉ መሆናቸውን ለመመርምር፤

ለ) አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ የደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ያቀረበው መረጃ ትክክለኛ ስለመሆኑ እና ይህንኑ የምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች ተሟልተው የቀጠሉ መሆናቸውን ለመመርምር፤

ሐ) ባቡሮችና የባቡር መሰረተ-ልማቶች ከባለሥልጣኑ የተሰጠና የፀና አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ ያላቸው መሆኑን እንዲሁም ይህንኑ ፈቃድ ሲያገኙ የነበራቸው ይዘትና የደህንነት ብቃት ያልተቀየረ መሆኑ ለማረጋገጥ የሚያስችል ምርመራ ለማድረግ፤

መ) ማንኛውም የባቡር ሥራ ባለሞያ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት ያቀረበው መረጃ ትክክለኛ ስለመሆኑ እና ይህንኑ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች ተሟልተው የቀጠሉ መሆናቸውን ለመመርምር፤

ይችላል፡፡

፫/ እውቅና በተሰጣቸው ተቋማት ላይ ለሚደረግ የኦዲትና ኢንስፔክሽን ተግባር የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው በተመሳሳይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፤ ሆኖም በእነዚህ ተቋማት ላይ የኦዲትና ኢንስፔክሽን ተግባራቱ ሊከናወኑ የሚችሉት

application of this Proclamation and regulations and directives issued pursuant to this Proclamation.

2/ Without limiting the generality of sub-article(1) of this Article any audit and inspection officer, without giving prior notice, by showing his identification, may enter into any railway infrastructure part or any train to:

a) inspect the genuineness of evidences furnished by infrastructure manager to obtain safety authorization and requirements to be fulfilled to obtain the authorization are still maintained;

b) inspect the genuineness of evidences furnished by railway undertaking to obtain safety certificate and requirements to be fulfilled to obtain the certificate are still maintained;

c) ensure the existence of a valid put in service license of trains and railway infrastructures as well as the conditions and safety capacity they had while obtaining the license is still maintained;

d) Inspect the genuineness of evidences furnished by any railway works professional to obtain competency license and requirements to be fulfilled to obtain the license are still maintained.

3/ For audit and inspection performed on accredited institute, the provision of this Article shall be applicable, as appropriate; provided, however, the audit and inspection on these institutes shall only be performed during official working days and hours.

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

በመደበኛ የሥራ ቀንና የሥራ ሰዓት ብቻ ይሆናል።

፴፩. **ጉድለት በተገኘ ጊዜ የኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን ሥልጣንና ኃላፊነት**

የኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን የዚህን አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ድንጋጌዎችን የሚቃረኑ ሁኔታዎች ወይም የባቡር ትራንስፖርት ደህንነትን አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ሁኔታዎች ባጋጠሙት ጊዜ እንደ አግባብነቱ፤

፩/ ጉድለቱ አነስተኛ እና ከፍተኛ የደህንነት ስጋትን የማይፈጥር ሆኖ ባገኘው ጊዜ እንደ አግባብነቱ የመሰረተ ልማት አስተዳዳሪው፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ፣ ወይም እውቅና የተሰጠው ተቋም ተገቢውን የእርምት እርምጃ ወዲያውኑ እንዲወሰድ ለማዘዝ፣ ወይም

፪/ ጉድለቱ ከባድ የሆነ እንደሆነ እና ከፍተኛ የደህንነት ስጋትን የሚፈጥር የሆነ እንደሆነ ጉድለቱ እስኪስተካከል ድረስ ወይም ተጨማሪ የማጣራት ስራዎች እስኪሰሩ ድረስ እንደአግባብነቱ፤

ሀ) አንድ ወይም ከአንድ በላይ ሎኮሞቲቮች፣ ፉርጎዎች ወይም የባቡር ስራ ባለሙያዎች ሥራ እንዲያቆሙ ለማዘዝ፤

ለ) አንድ የባቡር መስመርን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል አገልግሎት መስጠት እንዲያቆም ለማዘዝ፤ ወይም

ሐ) የመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪው፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ፣ ወይም እውቅና የተሰጠው ተቋም ተግባሩን ሙሉ በሙሉ እንዲያቆም ለማዘዝ፤

ይችላል።

31. Power and duties of the Audit and Inspection Officer when encountering defect

If the audit and inspection officer encounters conditions that breach the provisions of this Proclamation and regulations and directives issued under this Proclamation; or condition endangering railway transport safety, may order the following as the case may be:

1/ if he finds that the defect is minor and does not create a considerable safety threat, he may order the infrastructure manager, the railway undertaking or the accredited institute, as appropriate, to take the appropriate corrective measure immediately: or

2/ if the defect is serious and can create a considerable safety threat, he may order the following as the case may be:

a) suspension of operation of one or more than one locomotives, wagons or railway operation work professionals;

b) suspension of a railway line wholly or partly from service;

c) The infrastructure manager, railway undertaking or an accredited institute to stop their respective duties completely.

፴፪. **ከኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን ጋር የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም የመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ፣ አገልግሎት ሰጪ፣ እውቅና የተሰጠው ተቋም ወይም የባቡር ሥራ ባለሙያ የኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በሚያከናውንበት ወቅት፣

32. Duty to Cooperate with the Audit and Inspection Officer

Any infrastructure manager, railway undertaking, accredited institute or railway work's professional, while the audit and inspection officer exercise his duty and responsibility in accordance this Proclamation shall:

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

፩/ እንደ አግባብነቱ ወደ ባቡር መሠረተ-ልማቶች፣ ባቡሮች፣ እና ተቋማቱ እንዲገባና ምርመራ እንዲያደርግ የመፍቀድ፤

፪/ ተቀጣሪ ሠራተኞችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ጨምሮ ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መረጃዎችና ሰነዶችን እንዲመለከት የመፍቀድ፤

፫/ ከሥልጣንና ኃላፊነቱ ጋር በተያያዘ ለሚያቀርበው ጥያቄ በሚያውቀው መጠን ተገቢውንና እውነተኛ ምላሽ የመስጠት፤

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፩ መሰረት በኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንኑ የሚሰጥ ሕጋዊ ትዕዛዝን የመፈፀም፤

ግዴታ አለበት፡፡

ክፍል ስምንት

ስለባቡር የደህንነት ስጋት ክስተትና አደጋ ምርመራ

፴፫. ምርመራ የማድረግ ዓላማ

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት በመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ፣ በአገልግሎት ሰጪ ተቋም ወይም የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚከናወነው የባቡር የደህንነት ሥጋት ክስተት እና የባቡር አደጋ ምርመራ ዓላማዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፤

ሀ) የተከሰተን የደህንነት ሥጋት ክስተት ለማስወገድ የሚያስችል እርምጃ ለመውሰድ፤

ለ) ተመሳሳይ የደህንነት ሥጋት ክስተት እና የባቡር አደጋ እንዳይከሰቱ ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራትን ለማከናወን፤ እና

ሐ) ለደህንነት ሥጋት ክስተት ወይም ለባቡር አደጋ መከሰት መንስዔ የሆኑ ምክንያቶችን በማወቅ ተመሳሳይ የባቡር አደጋና የደህንነት ስጋት ክስተትን ለማስቀረት የሚያስችሉ እርምጃዎች ለመወሰድ፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለፁትን ዓላማዎች ለማሳካት የሚደረገው ምርመራ በሕግ

1/ permit the officer to enter into and inspect railway infrastructures, trains and institutes, as the case may be;

2/ permit the audit and inspection officer to inspect any relevant documents including documents related to its employees;

3/ give relevant and genuine response, to the extent he knows, to the questions raised in relation with the duties and responsibilities entrusted to him;

4/ respect legitimate order given by the audit and inspection officer in accordance with sub-article (4) of Article 31 of this Proclamation.

SECTION EIGHT

TRAIN SAFETY TREAT AND ACCIDENT INVESTIGATION

33. Purpose of Investigation

1/ Railway safety threat and train accident investigation conducted by infrastructure manager, railway undertaking or the body authorized by law to administer railway transport pursuant to this Proclamation shall have the following purposes:

a) to take action that enable to avoid safety threat that occurred;

b) to carry out activities that prevent the occurrence of similar railway safety threat and train accident; and

c) To carry out activities that avoid similar train accident and safety threat by identifying causes of safety threat or train accidents.

2/ The investigation conducted in order to achieve the purposes stated under sub-article (1) of this Article shall

0915735560

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

በተሰጠ ሥልጣን መሰረት በሌላ አካል የሚደረግ ምርመራን ሳይጠብቅ እና ሳይከተል ይከናወናል፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም የባቡር ደህንነት ስጋት ክስተት እና የባቡር አደጋን በተመለከተ የሚደረግ ምርመራ በሕግ ለሌላ አካል በተሰጠ ሥልጣን መሰረት የሚከናወን ምርመራን በማያደናቅፍ ሁኔታ መፈፀም ይኖርበታል፡፡

3/ Notwithstanding the provision of sub–article (2) of this Article, the investigation conducted on safety threat and train accident shall be carried out without affecting the investigation conducted by other body authorized by law.

፴፬. <u>የመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ እና አገልግሎት ሰጪ ተቋም ኃላፊነት</u>

34. <u>Responsibility of the Infrastructure Manager and Railway Undertaking</u>

፩/ ማንኛውም የመሠረተ ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም በባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ የደህንነት ስጋት ክስተት ወይም የባቡር አደጋ ሲያጋጥም ወዲያውኑ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል እና በአቅራቢያው ለሚገኝ የጸጥታ አካል ማሳወቅ አለበት፡፡

1/ Any infrastructure manager or railway undertaking shall inform promptly to the body authorized by law to administer railway transport and the nearby security body when safety threat or train accident is occurred on the railway transport service.

፪/ ማንኛውም የመሠረተ ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም የደህንነት ሥጋትን ለማስወገድ ወይም ሕይወትን ለማዳን ካልሆነ በስተቀር የፀጥታ ኃይሎች በቦታው እስኪደርሱ ድረስ ማስረጃዎች ሊያጠፉ የሚችሉ ተግባራትን መፈፀም የለበትም፡፡

2/ Any infrastructure manager or railway undertaking, unless to avoid the safety threat or to rescue life, shall not perform any activity which may misplace evidences until security bodies reach on the place.

፫/ ማንኛውም የመሠረተ ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም በሌላ ሕግ ሥልጣን የተሰጣቸው የፀጥታ አካላት የደህንነት ሥጋትንና የባቡር አደጋን በተመለከተ ምርመራ ሲያደርጉ በይዞታው የሚገኙትን መረጃዎች የመስጠትና ለሚቀርቡለት ጥያቄዎችም ትክክለኛ ምላሽ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

3/ Any infrastructure manager or railway undertaking shall have obligation to provide information under its possession; and give appropriate response to queries posed to him by legally authorized security bodies concerning safety threat and train accident.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የመሠረተ ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም የደህንነት ሥጋት ወይም የባቡር አደጋ ሲያጋጥም ተገቢውን ምርመራ የማድረግ፣ እንደ አግባብነቱ ክስተቱ ወይም

4/ Without prejudice to the provision of sub–article (1) and (2) of this Article, any infrastructure manager or railway undertaking shall have obligation to conduct appropriate investigation; as the case may be, submit detailed written

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

አደጋው መፈጠሩን ባወቀ በ፳፬ ሰዓት ጊዜ ውስጥ ዝርዝር መረጃዎችን የያዘ ሪፖርት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል በጽሁፍ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

report to the body authorized by law to administer railway transport within 24 hours as he knows from the occurrence of the safety threat or the train accident.

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሰረት የሚቀርብ ሪፖርት እንደ አግባብነቱ የደህንነት ሥጋቱን ወይም የባቡር አደጋውን ዝርዝር ሁኔታ፣ የተወሰደውን የመፍትሔ እርምጃና የተገኘውን ውጤት የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል፡፡

5/ The report submitted as per sub-article (4) of this Article shall specify the detail conditions of safety threat or train accident, actions taken as a solution and results obtained, as the case may be.

፮/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ ቢኖርም የደህንነት ስጋቱን ወይም የባቡር አደጋውን ዝርዝር መረጃና የተወሰደውን የመፍትሔ እርምጃ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ለማሳወቅ ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልግ በሚሆንበት ጊዜ የክስተቱን ወይም የአደጋውን መድረስ ብቻ የሚገልጽ መረጃ በማቅረብ ዝርዝር መረጃዎችንና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎችን የያዘ ሪፖርት የማጣራቱና እርምጃ የመውሰዱ ተግባር እንደተጠናቀቀ ለማቅረብ ይቻላል፣ ሆኖም አደጋው ከተከሰተ ከሰባት ቀን በላይ መብለጥ የለበትም፡፡

6/ Notwithstanding the provision of sub–article (4) of this Article, when additional time is needed to submit detailed report about the occurrence of the safety threat or the train accident or measures taken as a solution and its result, it is possible to inform only about the occurrence of safety treat or accident for the body authorized by law to administer railway transport and submit report of detailed information and actions taken as a solution as soon as the investigation and activity of taking measures are completed; provided, however, it shall not take more than seven days from the day of occurrence.

፯/ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፬) እና (፮) መሠረት ሪፖርት ሲደርሰው ወዲያውኑ ለሚኒስቴሩ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

7/ The body authorized by law to administer railway transport when receiving the report made in accordance with sub–article (1), (4) and (6) of this Article shall promptly inform the Ministry in writing.

፴፭. <u>የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ስለሚደረግ ምርመራ</u>

35. <u>Investigations of the Body Authorized by law to Administer Railway transport</u>

፩/ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፬ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፬) እና (፮) መሰረት ሪፖርት ሲደርሰው ሪፖርቱን በመመርመር፣

1/ The body authorized by law to administer railway transport after receiving the report made in accordance with sub–article (1), (4) and (6) of Article 34 and by examining it:

ሀ) የቀረበለትን ሪፖርትና የተወሰደውን የመፍትሔ እርምጃ ተቀብሎ ያፀደቀው እንደሆነ ይህንኑ ለባቡር መሠረተ ልማት አስተዳዳሪው ወይም

a) shall notify the infrastructure manager or railway undertaking if it accepts and approves the report and the action taken as a solution;

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

ለአገልግሎት ሰጪ ተቋሙ ማሳወቅ አለበት፤

ለ) በሪፖርቱና በተወሰደው የመፍትሔ እርምጃ ተገቢነት ላይ ጥርጣሬ ያደረበት እንደሆነ እንደ አግባብነቱ፣

(፩) ተጨማሪ መረጃዎች እንዲቀርቡለት፣ ተገቢ የሆነው የመፍትሔ እርምጃ እንዲወሰድ፣ ወይም ሌላ አግባብነት ያለውን ትዕዛዝ ለመስጠት፤ ወይም

(፪) በራሱ ሠራተኞች ወይም በሚወክለው ሌላ ባለሙያ የራሱን ምርመራ ለማድረግ፣

ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ማንኛውም ሞት ወይም አምስት እና ከአምስት በላይ በሆኑ ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ወይም ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ የንብረት ጉዳት ያስከተለ አደጋ መከሰቱን ባወቀ ጊዜ ምርመራ በማድረግ የራሱን ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት፡፡

፫/ ማንኛውም የመሠረተ ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ለ) (፪) እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል የራሱን ምርመራ ሲያደርግ በይዞታው የሚገኙትን መረጃዎች የመስጠትና ለሚቀርቡለት ጥያቄዎችም ተገቢውን ምላሽ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

b) if it has doubt on the appropriateness of the report and actions taken as a solution, as the case may be, it:

(1) may order additional information to be furnished, appropriate actions to be taken or give other relevant order which it believes appropriate; or

(2) May conduct its own investigation by its own employees or another expert appointed by it.

2/ Without prejudice to the provision of sub–article (1) of this Article, the body authorized by law to administer railway transport shall investigate and prepare its own report when it learns the occurrence of train accident that causes death, bodily injury of five or more persons, or property damage of more than One million Birr.

3/ Any infrastructure manager or railway undertaking shall furnish information under its possession; and give appropriate response to questions raised to it while the body authorized by law to administer railway transport conducts its own investigation as per sub-article (1) (b) (2) and sub-article (2) of this Article.

ክፍል ዘጠኝ
የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር እና ስለቅሬታና አቤቱታ አቀራረብ

SECTION NINE
POWERS AND DUTIES OF THE MINISTRY, HANDLING OF COMPLIANT AND PLEADING

፴፮. የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር

ሚኒስቴሩ የዚህን አዋጅ አፈፃፀም በተመለከተ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

36. Powers and Duties of the Ministry

The Ministry shall have the following powers and duties:

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

፩/ የባቡር ትራንስፖርትን የሚመለከቱ የፖሊሲ ሀሳቦችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ሕጎችን ማመንጨት፤ ከሌሎች የትራንስፖርት ዓይነቶች ጋር የተቀናጀ ሀገር አቀፍ የባቡር መሰረተ-ልማት ማስተር ፕላንን ማዘጋጀት፤ በመንግስት ሲፀድቁም ተፈፃሚነታቸውን ማረጋገጥ፤

1/ propose policy, strategies and laws concerning railway transport; prepare national railway infrastructure master plans integrated with other modes of transport, and ensure implementation of same upon approval by government;

፪/ አግባብነት ባለው ህግ በሚወሰነው መሰረት በባቡር መሰረተ ልማት ግንባታና በባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግ፤ በግሉ ዘርፍ ለሚከናወን የባቡር መሰረተ-ልማት ግንባታና ማስፋፊያ ፈቃድ መስጠት፤

2/ promote private sectors participation in railway infrastructure construction and railway transport service as determined by relevant law; provide license for new railway infrastructure construction and expansion carried out by private investors;

፫/ የመሰረተ ልማት አስተዳዳሪዎችንና አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን መመዝገብ፤

3/ register infrastructure mangers and railway undertaking;

፬/ ከጎረቤትና ሌሎች አገራት ጋር የባቡር ትራንስፖርትን በተመለከተ ከመንግስት በሚሰጥ አቅጣጫ መሰረት የመደራደር፤ የባቡር ትራንስፖርትን በተመለከተ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አፈፃፀም መከታተል፤

4/ negotiate, as per direction given by the government, agreements with neighboring and other countries concerning railway transport; follow-up the implementation of international railway transport agreements ratified by Ethiopia;

፭/ መንገደኞችና ዕቃዎች የሚጓጓዙበት ታሪፍ በውድድር ላይ የተመሰረተ እና ፍትሐዊ መሆኑን ማረጋገጥ እና ማጽደቅ፤

5/ ensure and approve transport tariffs set for passengers and goods are competitive and fair;

፮/ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር ከባቡር ትራንስፖርት ጋር የተያያዙ ትምህርትና ሥልጠናዎች እንዲሁም ጥናትና ምርምሮችና ቴክኖሎጂዎች የሚስፋፉበትን የሚያድጉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

6/ create favorable conditions for the expansion and development of railway transport educations and trainings, researches, and technologies in collaboration with higher education institutions;

፯/ ስለባቡር ደህንነት ለጎብረተሰቡ ሥልጠና መስጠትና ግንዛቤያቸውን ማሳደግ፤

7/ develop awareness of the public on railway safety through provision of training;

፰/ በዚህ አዋጅ መሠረት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠውን አካል የበላይ ኃላፊ በወሰናቸው ውሳኔዎች ላይ የቀረቡለትን አቤቱታዎችና ቅሬታዎች መመርመርና ውሳኔ መስጠት፤

8/ decide on pleadings and complaints submitted to it against decisions made by the head of the body authorized by law to administer railway as per this Proclamation;

፱/ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል በዚህ አዋጅ የተሰጡትን

9/ monitor the performance and proper discharge by the body authorized by law to administer railway transport

0915735560

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

ተግባርና ኃላፊነቶችን በአግባቡ እየተወጣ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

፴፮. ስለቅሬታ አቀራረብ

፩/ በኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን ወይም በሌላ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠውን አካል የሥራ ኃላፊ በዚህ አዋጅና አዋጁን መሠረት አድርገው በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት በተሰጡ ውሳኔዎች ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው የተሰጠውን ውሣኔ በመቃወም የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል የበላይ ኃላፊ ቅሬታ ለማቅረብ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርብ ቅሬታ ቅሬታው የሚቀርብበት ውሳኔ በተሰጠ ወይም ቅሬታ አቅራቢው የውሳኔውን መሰጠት ባወቀ በ፲፭ ቀናት ውስጥ የቅሬታውን ምክንያት በመግለጽ በጽሁፍ መቅረብ አለበት፡፡

፫/ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠውን አካል የበላይ ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሰረት ቅሬታ ሲቀርብለት ተጨማሪ ዝርዝር ማጣራቶችን ማድረግ የሚያስፈልግ ካልሆነ በስተቀር ቅሬታው በቀረበለት በ፲፭ የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠትና ለቅሬታ አቅራቢው በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፤ ተጨማሪና ዝርዝር ማጣራቶች ማድረግ የሚያስፈልግ ከሆነ በ፵፭ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት እና ለቅሬታ አቅራቢው ማሳወቅ አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት በተሰጠ ውሳኔ ያልረካ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፰ መሰረት ለሚኒስትሩ አቤቱታን ማቅረብ ይችላል፡፡

፴፯. ለሚኒስትሩ ስለሚቀርብ አቤቱታ

፩/ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠውን አካል በላይ ኃላፊ በዚህ አዋጅ

of its duties and responsibilities provided by this Proclamation.

37. Compliant procedure

1/ Any person who is aggrieved by a decision made by audit and inspection officer or by the officer of the body authorized by law to administer railway Proclamation, regulations and directives issued hereunder, may lodge his complaint to the head of the body authorized by law to administer railway transport by objecting the decision made.

2/ The complaint lodged pursuant to sub-article (1) of this Article shall be presented in writing by indicating the grounds of complaint within 15 days from the date of the decision or from the date that the complainant knew the decision.

3/ The head of the body authorized by law to administer railway transport, upon receiving the compliant in accordance with sub–article(2) of this Article, shall give decision within 15 working days from the date of receipt of the compliant and inform the decision to the complainant unless additional detailed investigation is required. If additional detailed investigation is required, he shall give a decision and inform it decision to the complainant within 45 days.

4/ Any person who is dissatisfied by decision passed in accordance with sub-article (3) of this Article may submit his pleading to the Minister as per Article 38 of this Proclamation.

38. Pleading to the Minster

1/ Any person who is dissatisfied by the activity performed or decision made by the head of the body

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ባከናወነው ተግባር ወይም በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው አቤቱታውን ለሚኒስትሩ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚቀርብ አቤቱታ ምክንያቶቹ ተገልፀውና በጽሁፍ ተዘጋጅተው የአቤቱታው ምክንያት የሆነው ተግባር በተፈፀመ ወይም ውሳኔ በተሰጠ ወይም የውሳኔው መሰጠት በታወቀ በ፴ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

፫/ ሚኒስትሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት አቤቱታ ሲቀርብለት ተጨማሪ ዝርዝር ማጣራቶችን ማድረግ የማያስፈልግ ከሆነ አቤቱታው በቀረበለት በ፳፩ የሥራ ቀናት ውስጥ፣ ተጨማሪ ዝርዝር ማጣራቶችን ማድረግ የሚያስፈልግ የሆነ እንደሆነ ደግሞ በ፷ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት እና ለአቤት ባዩ ውሳኔውን ማሳወቅ አለበት፡፡

፬/ ሚኒስትሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የይግባኙን ምክንያቶች እና የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠውን አካል ውሳኔ መርምሮ ውሣኔውን በማጽደቅ፣ በመሻር ወይም በማሻሻል ለይግባኝ ባዩ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሰረት የተሰጠ ውሳኔ የመጨረሻው አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሆናል፡፡

ክፍል አስር
የወንጀል ጥፋቶችና ቅጣቶች

፴፱. የፈቃድ አለመኖር

፩/ ማንኛውም ሰው

ሀ) የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ያልተመዘገቡ እና አገልግሎት ላይ የማዋል የፀና ፈቃድ ያልተሰጣቸው ሎኮሞቲቮች፣ ፉርጎዎች ወይም የባቡር መሰረተ ልማቶችን ለባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ያዋለ ወይም እንዲውሉ ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

authorized by law to administer railway transport, pursuant to the power given to him by this Proclamation may submit his pleading to the Minister.

2/ A pleading made in accordance with sub–article (1) of this Article shall be made in writing and indicating the grounds of pleading and be submitted within 30 days from the happening of the event, or decision made or the decision is known.

3/ The Minister, up on receiving the pleading in accordance with sub–article (2) of this Article, shall give decision within 20 working days from the date of receipt of the pleading and inform the decision to the pleader in writing unless additional detailed investigation is required. If additional detailed investigation is required, he shall give decision within 60 days and inform the decision to the pleader.

4/ The Minister, by investigating the grounds of pleading and the decision of the body authorized by law to administer railway transport, may approve, vary, or reverse the decision and notify the pleader in writing within the time provided under sub-article (3) of this Article.

5/ The decision made in accordance with sub–article (4) of this Article shall be a final administrative decision.

SECTION TEN
OFFENCES AND PENALITIES

39. Absence of Competency Certificate

1/ Any person who:

a) puts locomotives, wagons or railway infrastructures that are not registered by the ministry and not given competency license by the body authorized by law to administer railway transport service or make them put in service; or

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

ለ) በዚህ አዋጅ መሰረት የተሰጠው የፀና የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም የደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳይኖረው የመሠረተ ልማት አስተዳዳሪነት ወይም የአገልግሎት ሰጪነት ተግባርን ያከናወነ እንደሆነ

ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከሀያ ሺ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለፀው ጥፋት የሰው ህይወት መጥፋትን ወይም አካል መጉደልን ወይም ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ የሆነ የንብረት ጉዳትን ያስከተለ እንደሆነ ቅጣቱ ከሀያ ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከሁለት መቶ ሺ ብር በማያንስ ከአምስት መቶ ሺ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

b) undertakes infrastructure manager or railway undertaking works without having a valid safety authorization or safety certificate issued as per this proclamationshall be punished with rigorous imprisonment not exceeding ten years and fine not exceeding twenty thousand Birr.

2/ If the crime committed under sub-article (1) of this Article results in death or disability or property damage of more than one million Birr , the penalty shall be rigorous imprisonment not exceeding twenty years and fine not less than two hundred thousand Birr and not exceeding five thousand Birr.

፵. <u>የሀሰት ማስረጃ ስለማቅረብ</u>

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሰረት ምዝገባ ለማከናወን ወይም የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፣ የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ፣ አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ፣ የደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት፣ ወይም የእውቅና ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሀሰት ሰነዶችን ያቀረበ ወይም የተጠቀመ እንደሆነ ከሦስት ዓመት በማያንስ እና ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

፪/ ማንኛውም የመሰረተ ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም የደህንነት አስተዳደር ሥርዓቱን በተመለከተ ሀሰተኛ መረጃ ወይም ሪፖርት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ያቀረበ እንደሆነ ከሦስት ዓመት በማያንስ እና ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

40. <u>Producing fictitious Document</u>

1/ Any person who produces or uses fictitious document to obtain competency license, safety authorization, put in service license, safety certificate, accreditation certificate or for registration in accordance with this Proclamation shall be punished with rigorous imprisonment not less than three years and not exceeding seven years.

2/ Any infrastructure manager or railway undertaking which produce to the body authorized by law to administer railway transport fictitious evidence or false report concerning its safety management system shall be punished with rigorous imprisonment not less than three years not exceeding ten years.

፵፩. <u>የባቡር ትራንስፖርት ደህንነትን አደጋ ላይ ስለመጣል</u>

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ መሰረት በማድረግ በወጡት ደንቦችና መመሪያዎች ላይ

41. <u>Endangering Railway Transport Safety</u>

1/ Any person who breaches precautionary measures provided by this Proclamation and regulations and

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

የተደነገጉትን የጥንቃቄ ደንቦችን በመተላለፍ በተለይም በባቡር መሰረት ልማቶች አቅራቢያ የሚከናወኑ የግንባታ፣ የቁፋሮ ወይም ተመሳሳይ ሥራዎችን፣ ወይም የባቡር መሰረተ-ልማቶችን ከላይ ወይም ከስር አቋርጠው ወይም በትይዩ የሚከናወኑ መሰረተ-ልማቶችን በተመለከተ የወጡ ሕጎችን በመተላለፍ በባቡር ትራንስፖርት ላይ የደህንነት ስጋት እንዲፈጠር ያደረገ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከአንድ መቶ ሺ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

directives issued pursuant to this Proclamation; especially, carrying on construction, excavation or similar activities and construction of other infrastructures undertaken crossing or over passing or parallel to railway infrastructures; that creates safety threat on railway transport shall be punished with rigorous imprisonment of not exceeding five years and fine not exceeding one hundred thousand Birr.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተፈፀመው የወንጀል ድርጊት የባቡር አደጋ እንዲደርስ በማድረግ ሞትን ወይም ከባድ የአካል ጉዳትን አስከትሎ እንደሆነ ወይም ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት የንብረት ጉዳትን አስከትሎ እንደሆነ የእስራት ቅጣቱ እስከ ሀያ ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ይሆናል፡፡

2/ If the crime committed under sub-article (1) of this Article results in death or serious bodily injury or property damage of more than One Million Birr, the imprisonment punishment shall be rigorous imprisonment not exceeding twenty years.

፵፪. <u>ከአዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን ጋር አለመተባበር</u>

ማንኛውም ሰው የአዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን በዚህ አዋጅና አዋጁን መሰረት አድርገው በወጡት ደንቦችና መመሪያዎች የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ለማከናወን ወደ ሎኮሞቲቭ፣ ፉርጎ፣ የባቡር መሠረተ ልማት ወይም ዕውቅና ወደ ተሰጠው ተቋም እንዳይገባ የከለከለ እንደሆነ ወይም የአዲትና ኢንስፔክሽን መኮንኑ ለሚያቀርበው ጥያቄ በሚያውቀው መጠን ተገቢውንና እውነተኛ ምላሽ ያልሰጠ ወይም አግባብነት ያለውን መረጃ ለማሳየት ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከሀያ ሺ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

42. <u>Failure to Cooperate with Audit and Inspection Officer</u>

Whosoever refuse the audit and inspection officer to enter into locomotive, wagon or railway infrastructure, accredited institute; or did not give relevant and genuine response, to the extent he knows, or refuse to show the relevant document to the audit and inspection officer shall be punished with simple imprisonment of not exceeding one year and fine not exceeding twenty thousand Birr.

፵፫. <u>የባቡር የደህንነት ስጋት ክስተትንና የባቡር አደጋን አለማሳወቅ</u>

፩/ ማንኛውም የመሰረተ ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሰረት የባቡር ደህንነት ስጋት ወይም የባቡር አደጋ

43. <u>Failure to Report Safety Threat and Accident</u>

1 / Any infrastructure manager or railway undertaking, which fails to report the occurrence of safety threat and train accident to the body authorized by law to administer railway transport in accordance with the

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

መከሰቱን የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ያላሳወቀ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከሀያ ሺ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ የደህንነት ስጋት ክስተቱ ወይም የባቡር አደጋው ሪፖርት ያልተደረገው የባቡር መሰረተ ልማት አስተዳደሪውን ወይም የአገልግሎት ሰጭውን ወይም የሌላ ማናቸውንም ሰው ጥፋት ወይም ጉድለት እንዳይታወቅ ለመደበቅ በማሰብ የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከአንድ መቶ ሺ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል፡፡

፵፬. ተገቢ ምርመራ አለማድረግ ወይም ሀሰተኛ የምርመራ ሪፖርት ማቅረብ

ማንኛውም የመሰረተ ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም የባቡር ደህንነት ስጋት ክስተት ሲፈጠር ወይም የባቡር አደጋ ሲከሰት በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሰረት ተገቢውን ምርመራ ያላደረገ እንደሆነ ወይም ሀሰተኛ የምርመራ ሪፖርት ያቀረበ እንደሆነ ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከአንድ መቶ ሺ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል፡፡

፵፭. ሌሎች የወንጀል ጥፋቶች

ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎችን ወይም ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንብና መመሪያዎችን የተላለፈ ወይም አፈጻጸማቸውን ያሰናከለ እንደሆነ በቀላል እስራት ወይም በገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፵፮. የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በወንጀል የሚቀጣበት ሁኔታ

የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የዚህን አዋጅ ከአንቀጽ ፴፱ እስከ አንቀጽ ፵፭ ከተጠቀሱት ወንጀሎች አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑቱን የፈፀመ እንደሆነ ወይም ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንብና መመሪያዎችን የተላለፈ እንደሆነ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ ፴፬ በተደነገገው

provisions of this proclamation, shall be punished with simple imprisonment of not exceeding one year and fine not exceeding twenty thousand Birr.

2/ If the reason for failure to report the occurrence of safety threat or train accident is made with the intent to conceal the fault or defect of the infrastructure manager, railway undertaking the punishment shall be with rigorous imprisonment not exceeding five years and fine not exceeding one hundred thousand Birr.

44. **Performing Inappropriate Investigation Or Producing fictitious Investigation Report**

Any infrastructure manager or railway undertaking which fails to conduct the appropriate investigation on safety threat or train accident, in accordance with this Proclamation; or produces fictitious investigation report shall be punished with rigorous imprisonment not exceeding five years and fine not exceeding one hundred thousand Birr.

45. Other Offences

Whosoever violates or hinders the implementation of other provisions of this Proclamation or regulation and directives issued for the implementation of this Proclamation shall be punished with simple imprisonment or fine.

46. Criminally Liability of Judicial Person

If judicial person violates one or more provisions of Article 39 to 45 this Proclamation or regulations and directives issued as per this Proclamation, it shall be held criminally liable pursuant to conditions provided under Article 34 of the Criminal Code.

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

መሰረት ይቀጣል፡፡

ክፍል አስራ አንድ
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፵፯. ወንጀልን መከላከልና ምርመራ

በባቡር መሠረተ-ልማቶችና አገልግሎቶች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችንና የወንጀል ስጋቶችን ህብረተሰቡንና የሚመለከታቸውን የፌደራልና የክልል ተቋማትን በማስተባበር የመከላከልና ተፈጽመው ሲገኙም የመመርመር ሥልጣን የፌደራል የፀጥታ አካላት ነው፡፡

፵፰. የመተባበር ግዴታ

ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ማንኛውም ሰው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠውን አካል ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፵፱. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

፩/ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በነበረ ሕግ ወይም አሰራር መሰረት ፈቃድ አግኝቶ ይህ አዋጅ ተፈፃሚ የሚሆንባቸውን ተግባራት በማከናወን ላይ የሚገኝ ማናቸውም ሰው ሚኒስቴሩ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት እንደገና መመዝገብና አግባብነት ያላቸውን ፈቃድና የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት በሚኒስቴሩ የሚወሰነው ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ ቀደም ሲል በነበረው ሕግ ወይም አሰራር መሰረት ተሰጥተው የነበሩ አግባብነት ያላቸው ፈቃዶች ፀንተው ይቆያሉ፡፡

፶. የተሻሩ ድንጋጌዎችና አሰራሮች

፩/ የትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፰/፲፱፻፺፯ የአንቀጽ ፪ (፴፫) ፣ የአንቀጽ ፫ (፪)፣ የአንቀጽ ፯ (፬) ድንጋጌዎች እና የአንቀጽ ፳፫ (፩) "በኢትዮጵያ ሀዲዶች ላይ ባቡርን ማሽከርከር" የሚለው ሀረግ በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

፪/ የባቡር ትራንስፖርት ትራፊክ እና ደህንነት መቆጣጠሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር

SECTION ELEVEN
MISCELLANEOUS PROVISIONS

47. Prevention and Investigation of Crime

The federal security organs shall have the power to prevent risks of crime against railway infrastructures and services by coordinating the community, appropriate federal and regional organs, and to conduct investigation when crime is committed.

48. Obligations to Cooperate

Any person shall have the obligation to cooperate with the body authorized by law to administer railway transport for the implementation of this Proclamation.

49. Transitional Provisions

1/ Any person acquired a relevant license in accordance with existing laws or practice, before the coming into force of this Proclamation, to perform any activity governed by this Proclamation shall register and obtain necessary license or certificate again as per this Proclamation within the time frame determine by the Ministry.

2/ Registrations made or licenses given in accordance with laws and practices existed prior to this Proclamation shall remain valid until the end of the time-frame determined by the Ministry as per sub-article (1) of this Article.

50. Repealed Provisions and Practices

1/ The provisions of Article 2 (33), Article 3 (2), Article 7(4) and the phrase "or operate a train on Ethiopian railways" under Article 23(1) of the Transport Proclamation No. 468/2005 are hereby repealed by this Proclamation.

2/ The provisions of Article 24, 25, 26.27, 28 and 29 of the Railway Transport Traffic and Safety Control Council of

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

ቮ፻፸፫/፪ሺ፲ አንቀጽ ፷፬፣፷፭፣፷፮፣፷፯፣ ፷፰ እና ፷፱ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

ቮ/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፶፩. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ያወጣል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የወጡትን ደንቦች ለማስፈጸም መመሪያ ያወጣል፡፡

፶፪. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፱ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

Ministers' Regulations No. 348/2015 are hereby repealed by this Proclamation.

3/ No law or practice inconsistent with this Proclamation shall have effect with respect to matters provided by this Proclamation.

51. <u>Power to Issue Regulation and Directive</u>

1/ The Council of Ministers shall issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation:

2/ The Ministry shall issue directives for the implementation of this Proclamation and regulations issued pursuant to sub-article (1) of this Article.

52. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall come into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, on this 26th day of July 2017.

MULATU TESHOME (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

0915735560

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

0915735560

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

0915735560